30ኛ ዓመት ቁጥር 39
30th Year, No. 39

ባሕርዳር ሚያዝያ 15 ቀን 2018 ዓ.ም
Bahir Dar, April 23, 2026

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG
of the Amhara National Region Council in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the Auspices of the Council of the Amhara National Region

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 2228.47ብር
Unit Price Birr 2228.47

አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፮/፪ሺ፲፰ ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ

Proclamation No. 306/2026
The Revised Public Procurement and Property Administration Proclamation in the Amhara National Regional State

አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፮/፪ሺ፲፰ ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የክልሉ መንግሥት ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ሀብትን በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ፤

የዕቃዎች እና የአገልግሎቶች ግዥ እንዲሁም የግንባታ ሥራ ከመንግሥት ጠቅላላ ሀብት ከፍተኛውን የወጪ ድርሻ የሚይዝ በመሆኑ፣

የመንግሥት ግዥ በክልሉ ለሚከናወኑ የኢኮኖሚ ልማት ተግባሮች መስፋፋት አጋዥ መሣሪያ መሆን ስላለበት፣

ከፍተኛ ሀብት የሚፈስበት የመንግስት ንብረት በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲዉልና አሰተዳደሩም ዘመናዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የተቀናጀ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

Whereas, the efficient and effective use of resources is a fundamental issue for the regional government to effectively discharge its responsibilities;

Whereas, the procurement of goods and services and construction work constitute the largest portion of the total expenditure of the government;

Whereas, public procurement should be a tool for the expansion of economic development activities in the region;

Whereas, there is a need to establish an integrated system to ensure that public property, which are subject to high levels of investment, are better utilized and that their management is modernized;

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፱/፪ሺ፫ ዓ.ም ለረዥም ጊዜ ስራ ላይ የቆየ በመሆኑና አሁን ካለው የኢኮኖሚ እድገት እና የመግዛት አቅም ጋር እንዲጣጣም በማድረግ በአፈፃፀም ሲያገጠሙ የነበሩ ችግሮችንና የአሰራር ጉድለቶችን በማረም ወቅቱ ከደረሰበት የቴክኖሎጅ ለውጥ ጋር ለማራመድ የሚያስችሉ አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦች በማካተት መደንገግ በማስፈለጉ፤

የክልሉን መንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደሩን ዘመናዊ እንዲሆን ለማድረግ እና ግልፅ ፤ ፍትሀዊ ፤ አድሎ የሌለበት ፤ ተጠያቂነት የሰፈነበት እና የተጠያቂነት ወሰኑን በማስፋት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሀገር ውስጥ ተወዳዳሪዎችን በመንግስት ግዥ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ የበለጠ ለማበረታታትና በግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር ላይ በሚከሰቱ ችግሮች የሚያስከትለውን አስተዳደራዊ ተጠያቂነት እና የሕግ ተጠያቂነት ማስፈን አሰፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ሕገ - መንግሥት አንቀጽ ፶፱ ንኡስ አንቀጽ ፫(፩) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል፡፡

Whereas, the Amhara National Regional State Procurement and Property Administration Proclamation No. 179/2011 has been in force for a long time and it needs to be revised to reflect the current economic growth and purchasing power, correcting the problems and operational deficiencies that were encountered in its implementation and incorporating new concepts that will allow it to keep pace with the technological changes of the time;

Whereas, it is necessary to modernize the procurement and property administration of the regional government and to make it transparent, fair, non-discriminatory, accountable and applicable to public development organizations by expanding the scope of accountability;

Whereas, it is necessary to further encourage the participation of local candidates in public procurement and to establish administrative and legal liability for problems arising in procurement implementation and property administration;

The Amhara National Regional Council has issued this proclamation in accordance with the authority granted under Article 49, Sub-Article 3(1) of the Amhara National Regional Constitution.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፫፻፺/፪ሺ፲፰ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ግዥ" ማለት ዕቃዎችን፣ የምክር አገልግሎቶችን፣ ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶችን እና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን በመግዛት፣ በኪራይ፣ በሊዝ ስምምነት ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል ማግኘት ነው።

፪/ "ዕቃ" ማለት በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሳሪያ፣ ሸቀጥ፣ ለገበያ የተዘጋጀ ሶፍትዌር፣ እንስሳ እና ሌላ መሰል ነገሮችን ይጨምራል።

፫/ "ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት" ማለት ከግንባታ ዘርፍ ሥራ እና ከምክር አገልግሎት ውጪ የሆነ ማንኛውም አገልግሎት ሲሆን፣ የኪራይ፣ የትራንስፖርት፣ የህትመት፣ የጥገና፣ የጥበቃ፣ የጽዳት፣ የኃይል አቅርቦት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የውሃ አቅርቦት እና የመሳሰሉት አገልግሎቶችን ይጨምራል፤

፬/ "የዕቃ ዋጋ" ማለት አንድን ዕቃ ለማግኘት የሚከፈል አጠቃላይ ወጪ ሲሆን ከዕቃው ጋር ግንኙነት ያለውን እና ከዕቃው ዋጋ ያነሰ ዋጋ ያለው የተከላ፣ የትራንስፖርት፣ የጥገና እና ሌላ ተመሳሳይ ከምክር ውጪ የሆነ አገልግሎት ዋጋን እና ታክስን ይጨምራል፤

PART ONE

General Provisions

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Amhara National Regional State Public Procurement and Property Administration Proclamation No. 306/2026

2. Definition

Unless the context otherwise requires, the following definitions shall apply in this Proclamation:

1/ **"Procurement"** means the acquisition of goods, consultancy services, non-consultancy services and construction works by purchase, rental, lease agreement or any other similar contractual means.

2/ **"Good"** means raw materials, products, equipment, merchandise, software prepared for sale, livestock and other similar items in solid, liquid or gaseous form.

3/ **"Non-consultancy services"** means any service other than construction works and consultancy services, including rental, transportation, printing, maintenance, security, cleaning, power supply, telecommunications, water supply and other similar services;

4/ **"Price of good"** means the total cost of acquiring a good, including the cost of installation, transportation, maintenance and other similar non-consulting services related to the good and less than the price of the good, and taxes;

ሯ/ ‹‹የአገልግሎት ዋጋ›› ማለት አንድን ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ለማግኘት የሚከፈል አጠቃላይ ወጪ ሲሆን ከአገልግሎቱ ጋር የሚቀርብ ከአገልግሎቱ ዋጋ ያነሰ ዋጋ ያለውን ዕቃ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ዋጋን እና ታክስን ይጨምራል፤

ሷ/ ‹‹የምክር አገልግሎት›› ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚሰጡት የጥናት፣ የዲዛይን እና ቁጥጥር፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ለደንበኞች ምክር የመስጠት፣ ስልጠና የመስጠት እና እውቀትን የማስተላለፍ የመሳሰሉት የአማካሪነት ባህሪ ያለው የአዕምሮ አገልግሎት ነው፤

ቋ/ ‹‹የግንባታ ሥራ›› ማለት ከሕንጻ፣ ከመንገድ፣ ከድልድይ፣ ከግድብ፣ ከወደብ፣ ከውሃ ሥራዎች፣ ወይም ከሌሎች መሰረተ ልማት ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ ግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣ ደረጃ የማሳደግ፣ የማፍረስ፣ የጥገና ወይም የማደስ ሥራ ሲሆን የዲዛይን እና ግንባታ፣ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት፣ የተርንኪ እና የመሳሳሉ ውሎችን ይጨምራል፤

ቷ/ ‹‹የግንባታ ሥራ ዋጋ›› ማለት አንድን የግንባታ ሥራ ለማከናወን የሚከፈል አጠቃላይ ወጪ ሲሆን ከግንባታ ሥራው ጋር ተጓዳኝ የሆነ እና ከዋናው ሥራ ያነሰ ዋጋ ያለውን የአገልግሎት ዋጋን እና ታክስን ይጨምራል፤

ቿ/ **‹‹የመንግሥት መሥሪያ ቤት›› ማለት** ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግሥት በጀት የሚተዳደር ወይም በተቋቋመበት ሕግ የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ተቋም ተብሎ የተሰየመ የክልል መንግሥት አካል ሲሆን የክልሉ መንግሥት የልማት ድርጅቶችን እንዲሁም የመጠጥ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶችን ይጨምራል፤

5/ “Price of services” means the total cost of acquiring a non-consulting service, including the cost of goods or construction work provided with the service, less than the price of the service, and taxes;

6/ “Consulting services” means intellectual services of a consulting nature, such as research, design and supervision, organizing various projects, advising clients, providing training and transferring knowledge, provided by consultants using their professional skills;

7/ “Construction work” means the construction, reconstruction, upgrading, demolition, maintenance or renovation of a building, road, bridge, dam, port, waterworks or other infrastructure works, and includes design and construction, construction management, turnkey and similar contracts;

8/ “Price of Construction Work” means the total cost of carrying out a construction work, including the cost of services and taxes that are incidental to the construction work and are less than the cost of the main work;

9/ "Public Body" means a regional public body that is fully or partially funded by the regional public budget or is designated as a regional government office or institution by the law in which it was established, and includes regional government development organizations as well as drinking water and sewage service organizations;

፲/ ‹‹ **የመንግስት የልማት ድርጅት››** ማለት በክልል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ሕግ መሰረት የተቋቋመ ሆኖ ሙሉ በሙሉ በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሲሆን በክልሉ መንግስት የተቋቋመውን ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ እና በስሩ የሚተዳደሩ ድርጅቶችን አይጨምርም፤

፲፩/ ‹‹**የመንግሥት ገንዘብ››** ማለት የክልሉ መንግስት ከሰበሰበው ገንዘብ፣ከእርዳታና ብድር ያገኘው፤ ከፌደራል መንግሥት ከገኘው ድጎማ፤ ከውጭ እርዳታ እና ብድር የተገኘ ለመንግስት መስሪያ ቤት የተመደበ ገንዘብ ሲሆን በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን ገንዘብን ይጨምራል፤

፲፪/ ‹‹**የመንግሥት ግዥ››** ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የመንግሥት ገንዘብን በመጠቀም የሚያከናውኑት ግዥ ነው፤

፲፫/ ‹‹**ጨረታ››** ማለት የግዥ ወይም የንብረት ሽያጭ ማስታወቂያ ይፋ ከሆነበት ወይም ጥሪ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አሸናፊው ተለይቶ ውል እስኪፈረም ድረስ ያለው የግዥ አፈፃጸም ወይም የንብረት ሽያጭ ሂደት ነው፤

፲፬/ ‹‹**ተወዳዳሪ››** ማለት በመንግሥት ግዥ ወይም በንብረት ሽያጭ ላይ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም በጨረታ ለመሳተፍ ፍላጎት ያሳየ ሰው ነው፤

፲፭/ ‹‹**ተጫራች››** ማለት የመጫረቻ ሰነድ ያቀረበ ሰው ነው፤

10/ “Government -owned development enterprise” means a development enterprise established in accordance with the State-Owned Development Enterprises Act and wholly owned by the Regional Government, and does not include investment holding established by the Regional Government and organizations managed by it;

11/ “Public Fund” means funds collected by the regional government; funds received from grants and loans; subsidies received from the federal government; funds allocated to a government office from foreign grants and loans, and includes funds from development enterprises owned by the regional government;

12/ “Public procurement” means procurement carried out by public bodies using public funds;

13/ “Bid” means the process of procurement or sale of property from the time the notice of procurement or sale of property is published or called until the winner signs the contract;

14/ “Candidates” means a person who is invited to participate in a public procurement or sale of property or who has expressed an interest in participating in a bid;

15/ “Bidder” means a person who submits a bid proposal;

፲፮/ ‹‹አቅራቢ›› ማለት ለመንግሥት መሥሪያ ቤት ዕቃ ለማቅረብ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ለመስጠት ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራን ለማከናወን ውል የገባ ሰው ነው፤

16/ **“Supplier”** means a person who has entered into a contract to provide goods to a public body, to provide non-consulting services or to provide consulting services or to perform construction work;

፲፯/ ‹‹የግዥ ወይም የንብረት አስተዳደር ሙያተኛ›› ማለት በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ሕጎች መሰረት በግዥና ንብረት አስተዳደር ሙያተኞች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ ወይም የብቃት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤

17/ **“Procurement or Property Administration professional”** means a person who is registered in the list of procurement and property administration professionals or who has been issued a certificate of competency in accordance with this Proclamation and the laws issued to implement this Proclamation;

፲፰/ ‹‹የጨረታ ሰነድ›› ማለት በመደበኛ የጨረታ ሰነድ ላይ በመመስረት በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚዘጋጅ ዝርዝር የግዥ ፍላጎት መግለጫን ወይም በጨረታ የሚሸጡ ንብረቶችን ዓይነት እና ያሉበትን ሁኔታ እንዲሁም የመወዳደሪያ መስፈርቶችን የያዘ ሰነድ ነው፤

18/ **“Bid document”** means a document prepared by a public body based on a formal bid document containing a detailed statement of intent or the type and condition of the properties to be sold at auction, as well as the competition criteria;

፲፱/ ‹‹መደበኛ የጨረታ ሰነድ›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አጠቃላይ ይዘቱ አንድ ወጥ የሆነ ወይም ተመሳሳይ የሆነ የጨረታ ሰነድ በቀላሉ ማዘጋጀት እንዲችሉ የሚረዳ በቢሮዉ የሚዘጋጅ ሰነድ ሲሆን፣ ለዲዛይን እና ግንባታ፣ ለኮንስትራክሽን ማኔጅመንት፣ ለተርንኪ እና ለመሳሳሉ ውሎች የሚያገለግሉ ሰነዶችን ያካትታል

19/ **“Standard Bid Document”** means a document prepared by the bureau to facilitate the preparation of a uniform or similar bidding document for public bodies, and includes documents used for design and construction, construction management, turnkey and other contracts;

፳/ ‹‹የመጫረቻ ሰነድ›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ያዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ መሰረት በማድረግ ተጫራች በግዥው ወይም በሽያጩ ለመሳተፍ የሚያቀርበው የመወዳደሪያ ሀሳብ የያዘ ሰነድ ነው፤

20/ **“Bid Proposal”** means a document containing a competitive proposal submitted by a bidder to participate in the procurement or sale based on the bidding document prepared by the public body;

፳፩/ ‹‹ስትራቴጂያዊ ግዥ›› ማለት ክልላዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በቢሮዉ ውሳኔ በጥቅል የሚፈጸሙ ግዥዎች ናቸው፤

21/ “Strategic Procurement” means procurements that are made in bulk by the decision of the bureau due to their regional importance;

፳፪/ ‹‹የማዕከል ግዥ›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ያሏቸውን ተመሳሳይ የግዥ ፍላጎቶች በማጠቃለል በማዕከል የሚፈፀም ግዥ ነው፤

22/ “Central Procurement” means procurements that are made centrally by aggregating similar procurement needs of public bodies;

፳፫/ ‹‹የማዕቀፍ ስምምነት›› ማለት የረጅም ጊዜ አቅርቦትን ወይም ንብረት ማስወገድን ታሳቢ በማድረግ ወደፊት በሚፈጸም ዝርዝር ውል ለሚከናወን አቅርቦት ወይም ንብረት ለማስወገድ መሠረት በመሆን የሚያገለግል፣ በነጠላ ዋጋ እና ሌሎች የውል ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የሚፈፀም አጠቃላይ የሆነ ስምምነት ነው፤

23/ “Framework Agreement” means a general agreement that serves as the basis for a future detailed contract for the provision or disposal of goods or services, with a view to long-term supply or disposal of goods, and is based on a single price and other contractual terms;

፳፬/ ‹‹የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢ›› ማለት በማዕቀፍ ስምምነት ዕቃ ወይም ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ለማቅረብ ውል የገባ አቅራቢ ነው፤

24/ “Framework Agreement Supplier” means a supplier who has entered into a contract to provide goods or services other than consultancy services under a framework agreement;

፳፭/ ‹‹የመንግሥት ንብረት›› ማለት ከመንግሥት ገንዘብ እና መሬት በስተቀር የክልል መንግሥት ሀብት የሆነ ማንኛውም ንብረት ነው፤

25/ “Public Property” means any property that is the asset of a regional government, except for government funds and land;

፳፮/ ‹‹ቋሚ ንብረት›› ማለት ግዙፋዊ ሀልዎት ያለው፣ የተናጥል ዋጋው በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ገቢ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ ንብረት ነው፤

26/ “Fixed assets” means assets with material existence, the individual value of which is determined by the directives issued pursuant to this Proclamation, and which are used for a period of more than one year from the date of acquisition;

፳፯/ ‹‹ልዩ ቋሚ ንብረት›› ማለት ዋጋው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ለቋሚ ዕቃ ከተወሰነው ዋጋ ያነሰ ሆኖ ገቢ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ዕቃ ነው፤

27/ “Special fixed assets” means any asset whose value is less than the value determined by the directives issued by the Bureau for fixed assets and which is used for a period of more than one year from the date of acquisition;

፳፰/ ‹‹አላቂ ንብረት›› ማለት ከቋሚ ንብረት እና ከልዩ ቋሚ ንብረት ውጪ የሆነ ማናቸውም ንብረት ነው፤

28/ “Supplies” means any asset other than fixed assets and special fixed assets;

፳፱/ ‹‹የህይወት ዘመን ሥርዓት›› ማለት ከመንግሥት ንብረት ጋር የተያያዙ ተግባሮች እና ወጪዎችን የማቀድ፣ የመያዝ፣ የመረከብ፣ የመጠቀም፣ የጥገና፣ የፍጆታ ወይም የማስወገድ ወይም መዝገብ የመሰረዝ ተግባራትን ያካተተና የመንግሥት ንብረት አስተዳደር እና ቁጥጥር ብቃት ባለው መንገድ እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ነው፤

29/ “Life Cycle Approach” means a system that includes the activities and expenditures related to public property, including planning, holding, receiving, using, maintaining, disposing of, or decommissioning, and ensuring that public property is managed and controlled in an efficient manner;

፴/ ‹‹የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና›› ማለት የግዥውን መነሻ ዋጋ እና ንብረቱ አገልግሎት ላይ በሚውልበት፣ እንዲሁም እንደሁኔታው በሚወገድበት ጊዜ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ከባቢያዊ እና ማህበራዊ ወጪ የሚያካትት ትንተና ነው፤

30/ “Life-cycle cost analysis” means an analysis that includes the initial cost of the procurement and the economic, environmental and social costs incurred during the use of the asset, as well as its eventual disposal;

፴፩/ ‹‹ማስወገድ›› ማለት የመንግሥትን ንብረት በተለያየ ምክንያት ለመስሪያ ቤቱ ተገቢውን አገልግሎት የማይሰጥ ወይም በትርፍነት የሚገኝ ሆኖ ሲገኝ በሽያጭ፣ ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በማዛወር፣ በስጦታ ለሌላ አካል በማስተላለፍ፣ በማምከን፣ በማፈን፣ በመቀየጥ፣ በመቅበር ወይም በማቃጠል ከንብረት መዝገብ የመሰረዝ ተግባር ነው፤

31/ “Disposal” means the act of removing government assets from the asset register by selling, transferring to another public body, donating to another entity, sterilizing, stifling, converting, burying or burning them when they are no longer serving the purpose of the office or are no longer profitable;

፴፪/ ‹‹የውል አስተዳደር›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአቅራቢው ወይም ከሚወገድ ንብረት ገዥው ጋር ባሰረው ውል ላይ የተቀመጡ ግዴታዎች በአግባቡ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የሚከናወኑ የክፍያን፣ በወቅቱ የማስረከብን፣ የውል ማሻሻል፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የጥራትና መጠን ፍተሻን፣ የውል አለመግባባቶችን መፍታትን፣ ውል የማጠናቀቅ እና ሌሎች የውል አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር ተግባራትን ይጨምራል፤

32/ **“Contract Administration”** means the activities of the public body to ensure that the obligations set forth in the contract entered into with the supplier or purchaser of the property being disposed of are properly fulfilled, including payment, timely delivery, contract modification, price adjustment, quality and quantity inspection, resolution of contract disputes, contract completion and other contract performance monitoring and control activities;

፴፫/ ‹‹የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት›› ማለት የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ተግባራት የሚከናወንበት ሥርዓት ነው፤

33/ **“Electronic system”** means a system for conducting public procurement and asset administration activities using electronic means;

፴፬/ ‹‹የጥፋተኝነት ሪፖርት›› ማለት በግዥ ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጨረታ ሂደት ወይም ውል አፈፃፀም ሕጉን ያልጠበቀ ወይም የመሥሪያ ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት ወይም መታቀብ በፈፀመ ተጫራች ወይም አቅራቢ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ የመንግሥት መስሪያ ቤት ለቢሮዉ የሚያቀርበው ሪፖርት ነው፤

34/ **“Report of Default”** means a report submitted by a public body to the bureau to take administrative action against a bidder or supplier who has committed an act or omission that is contrary to the law or that is detrimental to the interests of the agency in the procurement or disposal of assets, or in the execution of a contract;

፴፭/ ‹‹ቢሮ›› ወይም ‹‹የቢሮ ኃላፊ›› ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገንዘብ ቢሮ ወይም የቢሮ ኃላፊ ነው

35/ **“Bureau”** or **“Head of Bureau”** means the Finance Bureau or Head of Bureau, respectively.

፴፮/ ‹‹የስራ አመራር ቦርድ›› ማለት በክልሉ መንግስት በባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች በበላይነት የሚመራ አካል ነው፡፡

36/ **“Board of Management”** mean a body that oversees development organizations owned by the regional government.

፴፯/ ‹‹ **ይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ አካል** ›› ማለት በመንግሥት መስሪያ ቤቶች የግዥ አፈጻጸም እና የንብረት አወጋገድ ሂደት ላይ በተወዳዳሪዎች፣ በተጫራቾች ወይም በአቅራቢዎች የሚቀርብለትን ይግባኝ መርምሮ ውሳኔ የሚሰጥ፣ ከፊል የዳኝነት ስልጣን ያለውና ሰያሜውም ወደፊት በመስተዳደር ምክር ቤቱ በሚወጣ ደንብ የሚገለፅ አካል ነው፤

፴፰/ ‹‹**አቤቱታ**›› ማለት ጨረታውን ያወጣው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ ወይም በሚወጡት በመንግሥትና የግል አጋርነት በአፈጻጸም መመሪያዎች የተመለከተውን ባለመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት ወይም በደል ደርሶብኛል ወይም ሊያደርስብኝ ይችላል የሚል ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚያቀርበው ቅሬታ ነው፤

፴፱/ ‹‹**የተርንኪ ግዥ**›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተናጥል ሊፈፀሙ የሚችሉ የአንድ ፕሮጀክት አካል የሆኑ ግዥዎችን በማቀናጀት በአንድ ጨረታ የሚፈፅሙበት የግዥ ሥልት ነው፤

፵/ ‹‹**ልዩ አስተያየት**›› ማለት በመንግሥት የግዥ ሂደት ለሀገር ውስጥ ምርቶች፣ ለኢትዮጵያውያን ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ሰጪዎች፣ አማካሪዎች፣ ሥራ ተቋራጮች፣ እና ልዩ ትኩረት ለሚሹ የሥራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሰረት ልዩ አስተያያት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለተገለፀ አካላት በውድድር ወቅት የሚሰጥ የተለየ ድጋፍ ነው።

፵፩/ ‹‹**የታከለ እሴት**›› ማለት አንድ የሀገር ውስጥ ምርት ለገበያ ከመቅረቡ በፊት በምርቱ ላይ በሀገር ውስጥ የታከለው ተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ እሴት ነው።

37/ "Appeals and Decision-Making Body" means a body that examines and decides on appeals submitted by competitors, bidders or suppliers in the procurement and property disposal processes of public bodies, has quasi-judicial powers, and its name will be determined by a regulation issued by the Governing Council in the future;

38/ "Complaint" means a complaint submitted to the head public body that issued the bid by a candidator or bidder alleging that he has suffered or may suffer harm or injustice due to the failure of the public body that issued the bid to comply with the provisions of this proclamation or the directives for the implementation of the public-private partnership;

39/ "Turnkey procurement" means a procurement method in which public bodies combine procurements that are part of a project that could be made separately and make them a single bid;

40/ "Margin of Preference" It means special support provided during the competition period for domestic products, non-consulting service providers, consultants, contractors, and job creation institutions that require special attention in the public procurement process, as well as for entities that have been declared to benefit from special considerations under this proclamation.

41/ "Value added" means the additional economic value added domestically to a domestic product before it is put on the market.

፵፪/ **"የሊዝ ስምምነት"** ማለት የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በግዥ ምትክ ወጪ ሊቆጥቡ የሚችሉ፣ ተለዋዋጭነት እና የቅርብ ጊዜ ቴክኖሎጂን መጠቀም የሚያስችሉ ንብረቶችን በኪራይ ለተወሰነ ጊዜ ማግኘት የሚችሉበት የውል ስምምነት ነው።

42/ **"Lease agreement"** means a contractual agreement under which public bodies can obtain assets on rent for a specified period of time that can save costs, allow flexibility, and utilize the latest technology instead of purchasing them.

፵፫/ **"የተገደበ ጨረታ "** ማለት ለዕቃው፣የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር አገልግሎቱ ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ስለመሆኑ መረጃ ያለ እንደሆነ የተመረጡ ውስን አቅራቢዎችን በመጋበዝ አገልግሎቶችን መግዛት አስፈላጊ መሆኑ ሲታመን የሚፈጸምበት የግዥ ዘዴ ነው።

43/ **"Restricted Bidding"** means a procurement method where it is deemed necessary to procure services by inviting a limited number of selected suppliers, where there is information that the goods, works, consultancy services or other services are available only from certain suppliers.

፵፬/ **"የግዥ ዘዴ"** ማለት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ስራዎችን፣ ምክር ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ወይም የምክር አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያስችላቸዉ ዘዴ ነው።

44/ **"Procurement method"** means a method by which goods, works, non-consulting services or consultancy services are procured.

፵፭/ **"የግዥ ስልት"** ማለት በግዥ አቀራረብ ወቅት አንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ሥራዎችን፣ ምክር ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ወይም የምክር አገልግሎቶችን ለማግኘት በጣም ተስማሚ የሆኑትን ዘዴዎች ወይም ስርዓቶች ለመምረጥ የሚጠቀምበት አጠቃላይ ስልታዊ ሂደት ማለት ነው።

45/ **"Procurement Approach"** means the overall strategic process by which a public body, during a procurement process, selects the most appropriate methods or systems for procuring goods, works, non-consulting services or consultancy services.

፵፮/ **"የሐራጅ ሽያጭ"** ማለት ገዥዎች ዋጋን በመጨመር የሚወዳደሩበት ሂደት ሲሆን መንግስት መስሪያ ቤቱ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ገዥ ውሉን የሚሰጥበት ነው።

46/ **"Auction sale""** means a process in which buyers compete by increasing the price and the public body awards the contract to the buyer who offers the highest price.

፵፯/ ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

47/ **"Person"** means a natural or legal person.

፵፰/ በዚህ አዋጅ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

፫. የተፈጻሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ በማንኛውም በክልሉ በሚገኙ የክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መንግሥት ከፌዴራል መንግስትም ሆነ ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ የሌሎች ሀገር መንግሥታት ወይም ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ካደረገው ወይም ከሚያደርገው ስምምነት ወይም ከስምምነቱ ከመነጨ ግዴታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በስምምነቱ የተመለከተው ግዴታ ተፈፃሚ ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት ልማት ድርጅቶች ከሆኑት በስተቀር የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከሌሎች የመንግስት መሰሪያ ቤቶች እቃ ወይም አገልግሎት ለማግኘት በሚያደርጉት ውል ይህ አዋጅ ተፈፃሚ አይሆንም።

፬. መርሆች

የመንግሥት ግዥ አፈፃጸም እና የንብረት አስተዳደር የሚከተሉትን መርሆች መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡

፩/ የመንግሥት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፤

፪/ አድልዎ አለማድረግ፤

፫/ ግልጽነት እና ፍትሐዊነት፤

48/ Any reference in this Proclamation to the masculine gender includes the feminine gender.

3. Scope of Application

1/ This Proclamation shall apply to the procurement and property administration of any public body in the region.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1 of this Article, if it is inconsistent with any agreement or obligation that the government of the region has made or will make with the federal government or with one or more foreign governments or international organizations, the obligation specified in the agreement shall apply.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1 of this Article, this Proclamation shall not apply to contracts entered into by government offices, other than government development organizations, to obtain goods or services from other government offices.

4. Principles

The implementation of public procurement and property administration should be based on the following principles:

1/ Value for money in the use of public fund;

2/ To be non-discriminatory;

3/ Transparency and fairness;

፬/ በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያስከትል፣ እንዲሁም የህይወት ዘመን ወጪ ትንተናን ከግምት ያስገባ እና መልሶ መጠቀምን የሚያበረታታ፤

፭/ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ፤

፮/ ተግባራትን በታማኝነት መፈፀም፤

፯/ ተጠያቂነት፤

፰/ የቴክኖሎጂ ፈጠራን ማበረታታት።

4/ Environmentally friendly, taking into account life-cycle cost analysis and encouraging reuse;

5/ Efficient, effective and cost-effective;

6/ Performing tasks with integrity;

7/ Accountability;

8/ Encouraging technological innovation.

ክፍል ሁለት

ተግባርና ኃላፊነት

፭. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ተግባር እና ኃላፊነት

የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ በመሥሪያ ቤቱ የሚፈጸሙ ግዥዎች እና የንብረት አስተዳደር ተግባራት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ተከትሎ በዕቅድ የተመሰረቱ እና በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መርሆችን በጠበቀ መንገድ መተግበራቸውን የማረጋገጥ፤

፪/ የግዥና ንብረት አስተዳደር የስራ ተግባራትን የሚያከናውኑ የስራ ክፍሎችን በማደራጀት ለስራው የሚያስፈልጉ ሙያተኞችን መመደብ፤

፫/ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ የመሥሪያ ቤቱ የፕሮጀክት ግዥዎች ከመፈጸማቸው አስቀድሞ የግዥ ፕሮጀክት ስትራቴጅ የተዘጋጀላቸው መሆኑን የማረጋገጥ፤

PART TWO

Duties and Responsibilities

5. Duties and Responsibilities of Head of a Public Body

The Head of public body shall have the following duties and responsibilities:-

1/ To ensure that the procurement and property adminstration activities carried out by the office are carried out electronically in accordance with the procurement and property adminstration principles established in the plan and referred to in this Proclamation;

2/ Organizing work units that perform procurement and asset management tasks and assigning the necessary professionals to the work;

3/ To ensure that a procurement project strategy is prepared for the procurement of high-cost projects of the office before they are carried out;

፬/ መሥሪያ ቤቱ የሚኖረውን የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራት ባህርይ ከግምት በማስገባት እንደ አስፈላጊነቱ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ የማቋቋም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውስብስብ ለሆኑ ግዥዎች ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ፣ እንዲሁም የንብረት ዋጋ ገማች ኮሚቴ የማቋቋም፤

4/ To establish one or more procurement and disposal endorsing committees as necessary, taking into account the nature of the procurement and property management activities of the office, and to establish an ad hoc procurement review committee for complex procurements, as well as property valuation committee, when necessary;

፭/ በግዥ እና በንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ የሚመደቡ ወይም የተመደቡ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሙያተኞች፣ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሰረት የሚቋቋሙ ኮሚቴዎች አባላት ይህንን አዋጅ፣ የአፈፃጸም መመሪያዎችን፣ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ማንዋሎችን፣ መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን፣ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት አጠቃቀም እንዲያውቁ ማድረግ የሚያስችል ስልጠና ማግኘታቸው እና የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን ለመፈጸም በቂ እውቀት እና ክህሎት ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ፤

5/ Ensuring that procurement and property administration professionals, employees and officers assigned or assigned to procurement and property administration work, as well as members of committees established under Sub-Article 4 of this Article, receive training to familiarize them with this Proclamation, implementation directives, procurement and property administration manuals, standard bidding documents, and the use of electronic systems, and have sufficient knowledge and skills to carry out government procurement and property administration;

፮/ መሥሪያ ቤቱ በተከናወነ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ኦዲት የተለዩ የአሰራር ግድፈቶች የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው የማድረግ እና የአፈጻጸም ሂደቱን አስመልክቶ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት መላኩን የማረጋገጥ፤

6/ To ensure that corrective action is taken on operational deficiencies identified in the procurement and property administration audit conducted by the office and to ensure that a report is sent to the relevant bodies regarding the implementation process;

፯/ መሥሪያ ቤቱ ባለው አደረጃጀት ምክንያት የተለያዩ ማዕከላት ያለው ሲሆንና ስራዎችን በአግባቡ ለመወጣት ያመቻል ብሎ ሲያምን ማዕከላቱን በበላይነት ለሚመሩ ኃላፊዎች ከግዥ ዕቅድ ዝግጅት ውጭ ያሉ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ስራዎችን እንዲመሩ፣ እንዲያስፈጽሙ ውክልና የመስጠት

7/ To delegate to the heads of the centers, when the office has various centers due to its organization and believes that it will be able to carry out the tasks properly, to direct and execute procurement and property administration tasks other than the procurement plan preparation;

፰/ በአጽዳቂ ኮሚቴ መጽደቅ የማያስፈልጋቸውን ግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ እንዲያጸድቅ ለግዥ እና ንበረት አስተዳደር ተግባራትን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ውክልና የመስጠት፤

8/ To delegate to the department performing procurement and property administration tasks to endorse the procurement and disposal of property that do not require approval by the endorsing committee;

፱ / የቀጥታ ግዥ ዘዴን ለመጠቀም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፮ ላይ የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲሟሉና ግዥውን በቀጥታ መፈፀም ለመሥሪያ ቤቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑን ሲያምን ግዥው በቀጥታ እንዲፈፀም የመወሰን፤

9 / To decide to use the direct procurement method when the conditions set out in Article 26 of this Proclamation are met and when it is believed that direct procurement will bring economic benefits to the office, to make the procurement directly;

፲/ በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎች መሠረት የግዥ ዕቅድ፣ የግዥ አፈፃፀም፣ የተሸከርካሪና ነዳጅ አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች ለገንዘብ ቢሮ መቅረብ ያለባቸው ሪፖርቶች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ መሰረት ወቅቱን ጠብቀው መቅረባቸውን የማረጋገጥ፤

10 / To ensure that the procurement plan, procurement performance, vehicle and fuel usage, and other reports to be submitted to the Finance Office are submitted in a timely manner through the electronic system in accordance with this Proclamation and the detailed implementation directives to be issued for the implementation of this Proclamation;

፲፩/ በመሥሪያ ቤቱ የሚገኝ የመንግሥት ንብረት ተገቢው ጥበቃ እና እንክብካቤ የሚደረግለት እንዲሁም የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋለት መሆኑን የማረጋገጥ፤

11 / To ensure that government property in the office is properly protected and cared for and that a monitoring and control system is in place;

፲፪/ የግዥና የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍሎች፣ የግዥና የሚወገዱ ንብረቶች አፅዳቂ ኮሚቴ እና ሌሎች ግዥን የመፈፀም እና ንብረትን የማስወገድ ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ተግባራቸውን በተገቢው ሁኔታ መወጣታቸውን የማረጋገጥ፤

12/ To ensure that the Procurement and property administration Departments, the Procurement and property Disposal Endorsing Committee and other bodies responsible for procurement and property disposal perform their duties properly;

፲፫/ እንደአስፈላጊነቱ የመሥሪያ ቤቱን የግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል በሦስተኛ ወገን የማሰራት፤

13/ To outsource all or part of the procurement and property administration activities of the Office to third parties as necessary;

፲፬/ መሥሪያ ቤቱ በሚፈፅመው ግዥ እና በንብረት ማስወገድ ሂደት ላይ ለሚቀርብ አቤቱታ አጣርቶ ምላሽ መስጠት፣ እንዲሁም በይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ አካል የሚተላለፍ ውሳኔን ተፈፃሚ የማድረግና ስለአፈፃፀሙ ለዚሁ አካል ሪፖርት የማቅረብ፤

፲፭/ በግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ሂደት ይፋ መደረግ ያለባቸው መረጃዎች ወቅቱን ጠብቀው በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ዘዴዎች ለሕዝብ ይፋ መደረጋቸውን የማረጋገጥ፡፡

፮. የግዥ እና የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት

በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የሚቋቋሙት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍሎች የሚኖሯቸው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡ መመሪያዎች የሚወሰኑ ሆነው የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፡-

፩/ የመሥሪያ ቤቱ ተግባራት ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር እንዲጣጣም፣ እንዲሁም ውጤታማ የሆነ የበጀት ዝግጅት ለማድረግ እንዲያመች የግዥ ዕቅድ በወቅቱና በአግባቡ ማዘጋጀትና በዕቅዱ መሰረት ግዥውን መፈጸም፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ በተደነገገው መሰረት ከሚመለከታቸው የመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች ጋር በጋራ በመሆን ከፍተኛ ወጪ ለሚጠይቁ የመሥሪያ ቤቱ ግዥዎች ፕሮጀክት እቅድ ማዘጋጀት እና አፈፃፀሙን መከታተል፣

14/ Investigating and responding to complain submitted to the Office regarding the procurement and disposal of property, as well as enforcing decisions issued by the appeals and decision-making body and reporting to this body on its implementation;

15/ Ensuring that information required to be disclosed during the procurement and sale of property to be disposed of is made public in a timely manner through the electronic system and other appropriate means.

6. Duties and Responsibilities of Procurement and Property Administration Units

The detailed duties and responsibilities of the Procurement and Property Administration Units established in public body shall be determined by the directives issued pursuant to this Proclamation and shall have the following general duties and responsibilities:-

1/ To prepare a procurement plan in a timely and proper manner so that the activities of the office are in line with the financial plan and to facilitate effective budget preparation and to carry out the procurement in accordance with the plan;

2/ To prepare a project plan for the procurement of the office that requires high costs in collaboration with the relevant departments of the office in accordance with the provisions of Article 5, Sub-Article (3) of this Proclamation and to monitor its implementation;

፫/ ይህንን አዋጅ፣ የአፈፃፀም መመሪያዎችን፣ መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን እና ሌሎች የአሰራር ሰነዶችና ቅጾችን እንዲሁም የግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ውሎችን መሠረት በማድረግ የመንግሥት ግዥን እና ንብረት አስተዳደርን በተሟላ የሙያ ሥነ-ምግባር እና ክህሎት የመፈፀም፤

፬/ በቢሮው ከሚወገዱ ንብረቶች ውጪ ያሉትን መወገድ ያለባቸውን የመሥሪያ ቤቱን ንብረቶች ይህንን አዋጅ፣ የንብረት አስተዳደር መመሪያውን፣ ሌሎች የአሰራር ሰነዶች እና ቅጾችን መሠረት በማድረግ አግባብነት ባለው የንብረት ማስወገጃ ዘዴ የማስወገድ፤

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ በተደነገገው መሠረት የተሟላ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት የመያዝ፤

፮/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ውስጥ ራሱን የቻለ የውል አስተዳደር የሥራ ክፍል ከሌለ የውል አስተዳደር ሥራዎችን የማከናወን፤

፯/ የአቅራቢዎችንና የሚወገድ ንብረት ገዥዎችን የውል አፈፃፀም ብቃት የሚያሳዩ መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሰረት የመያዝ።

፯. የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች አፅዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፬) የሚቋቋመው የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች አጽዳቂ ኮሚቴ የሚኖረው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ቢሮዉ በሚያወጣቸው መመሪያዎች የሚወሰን ሆኖ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖረዋል፡-

3/ To carry out public procurement and property administration with full professional ethics and skills in accordance with this Proclamation, the Implementation Directives, the Standard Bidding Documents and other procedural documents and forms, as well as the procurement and sale contracts of property to be disposed of;

4/ To dispose of the Properties of the office that are to be disposed of, other than the properties disposed of by the bureau, by appropriate Property disposal methods in accordance with this Proclamation, the Property Administration Directives, other procedural documents and forms;

5/ To maintain complete procurement and property administration information in an electronic system as provided for in Article 11 of this Proclamation;

6/ To perform contract management functions in the absence of a separate contract administration department within the public body;

7/ To maintain information on the performance of suppliers and buyers of property to be disposed of in an electronic system.

7. Duties and Responsibilities of the Procurement and Disposal Endorsing Committee

The Procurement and Disposal Endorsing Committee established under Article 5, Sub-Article (4) of this Proclamation shall have the following main duties and responsibilities, as determined by the directives issued by the Bureau:

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፮ መሠረት ከሚፈፀሙ ቀጥታ ግዥዎች ውጪ፣እንዲሁም በግዥ አፈፃፀም መመሪያው ለዋጋ ማቅረቢያ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ ግዥዎች አፈፃፀምን በተመለከተ ከግዥ ሥራ ክፍል የሚቀርብለትን የውሳኔ ሀሳብ ሌሎች ይህንን አዋጅ፣ የግዥ መመሪያን፣ መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን እንዲሁም የአሰራር ሰነዶችና ቅጾችን መሠረት በማድረግ መርምሮ ማጽደቅ፣የአሰራር ስህተት ያለበት ከሆነ እንደሁኔታው ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግበት ጉዳዩን ለግዥ ክፍሉ መልሶ መላክ ወይም ሂደቱ እንዲሠረዝ መወሰን፤

1/ To examine and approve the proposal submitted by the Procurement Division regarding the implementation of procurements exceeding the amount of money specified in the Procurement Implementation Directives, other than direct procurements carried out in accordance with Article 26 of this Proclamation, based on this Proclamation, Procurement Directives, standard bidding documents, and procedural documents and forms; if there is a procedural error, to refer the matter back to the Procurement Division for appropriate corrections, as the case may be, or to decide to cancel the process;

፪/ በቢሮው ከሚወገዱ ንብረቶች በስተቀር ከንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍል በሚቀርብለት የውሳኔ ሀሳብ መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ ይህንን አዋጅ፣ የንብረት አስተዳደር መመሪያን፣ እንዲሁም ሌሎች የአሠራር ሰነዶችና ቅጾችን መሠረት በማድረግ መርምሮ ማጽደቅ፣ የአሰራር ስህተት ያለበት ከሆነ እንደሁኔታው ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግበት ጉዳዩን ለንብረት አስተዳደር ክፍሉ መልሶ መላክ ወይም ሂደቱ እንዲሰረዝ መወሰን፤

2/ To examine and approve the sale of public body Property to be disposed of, except for properties disposed of by the office, in accordance with this proclamation, the Property Administration Directives, and other operational documents and forms, and if there is a procedural error, to refer the matter back to the Property Administration Division for appropriate corrections or to decide to cancel the process;

፫/ የመንግሥት ግዥን እና ንብረት አወጋገድን ውጤታማ ለማድረግ በሚያስችሉ ዘዴዎች ላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን የበላይ ኃላፊ ማማከር፤

3/ To advise the head of public body on methods that can make public procurement and property disposal more effective;

፬/ በመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍል የሚዘጋጀውን ዓመታዊ የግዥ እና የንብረት ማስወገድ ዕቅድ በመመርመር ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አስተያየት ማቅረብ፤

4/ To examine the annual procurement and property disposal plan prepared by the office's operational department and to provide comments to the head of the office;

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት በሥራ አመራር ቦርድ ለሚተዳደሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዥው በመሥሪያ ቤቶቹ የስራ አመራር ቦርድ እንዲጸድቅ የግንዘብ ቢሮ ኃላፊ በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፰. ተጠያቂነት

መንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ፣ የመንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍሎችን የሚመሩ ኃላፊዎች፣ ለግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥራ የተመደቡ ሠራተኞች፣ ባለሙያዎች፣ እንዲሁም የግዥ አጽዳቂ እና የንብረት አስወጋጅ እና ሌሎች ኮሚቴዎች አባላት ስለሚወስዷቸው ይህንን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን ያልጠበቁ እርምጃዎች የሕግ እና የአስተዳደር ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

ክፍል ሦስት

የግንዘብ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

፱. የቢሮው ሥልጣን እና ተግባር

አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ለቢሮው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር ፖሊሲዎች፣ መርሆችና አፈፃፀም ላይ የክልሉን መንግሥት ማማከር፣ ለቢሮዎች፣ ለክልል ተጠሪ መ/ቤቶች ለወረዳዎች፣ ለከተማ መስተዳደሮች እና ለክልሉ መንግስት ልማት ድርጅቶች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤

5/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this article, the Head of the Finance Bureau may, in exceptional circumstances, authorize the approval of the Board of Directors of the public bodies managed by the Directorate Board due to the nature of their work.

8. ACCOUNTABILITY

The head of public body, heads of public procurement and property administration departments, employees assigned to procurement and property administration, experts, as well as members of the procurement endorsing and property disposal committee and other committees, shall be held legally and administratively liable for actions taken by them that do not comply with this proclamation and the directives issued pursuant to this proclamation.

PART THREE

Duties and Responsibilities of the Finance Bureau

9. Powers and Duties of the Bureau

Without prejudice to the powers and duties assigned to the Bureau by other relevant laws, the Bureau shall have the following powers and duties:

1/ To advise the regional government on public procurement and property administration policies, principles and implementation, and to provide technical assistance to offices, regional offices, weredas, urban administrations and regional government development organizations;

፪/ በመንግሥት ግዥ አፈፃፀምና ንብረት አስተዳደር ሥርዓትና አተገባበር ላይ ጥናት ማከናወን እንዲሁም በጥናቱ ላይ ተመስርቶ ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ መመሪያዎችን ማሻሻል፤

2/ To conduct research on the implementation of public procurement and property administration systems and to modify directives based on the research and recommendations for improvement of the system;

፫/ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቀርብለትን መረጃ መሰረት በማድረግ የመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት አፈፃፀምን በሚመለከት የተጠቃለለ አመታዊ ሪፖርት ለክልሉ ምክር ቤት ማቅረብ፣

3/ To submit a comprehensive annual report to the regional council on the implementation of the public procurement and property administration system based on information provided by public bodies.

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር የተዘረዘሩትን ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚያስጠይቁ ጥፋቶች የፈፀመ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተሿሚ ወይም የተመደበ ሰው ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲወሰን ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ፤

4/ To submit to the relevant bodies for the imposition of administrative penalties on any person appointed or assigned to a public body who has committed any of the offenses listed in Article 65, Sub-Article (2) of this Proclamation;

፭/ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚፈለጉ ተመሳሳይ ንብረቶች ደረጃ ማውጣትና የወጡት ደረጃዎች ወጥነት ባለው መንገድ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣

5/ To establish standards for similar assets required by public bodies in cooperation with relevant public bodies and to ensure that the standards are implemented in a consistent manner;

፮/ የግዥና ንብረት አስተዳደር የሕግ ማዕቀፍን ሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ ማፅደቅ፣ የግዥ ዝርዝርና ካታሎግ ልዩ ልዩ ቅፆችን፣ ማኑዋሎች እንዲሁም የግዥና ንብረት ሙያተኞች እና ኃላፊዎች ሊከተሏቸው የሚገባ የሥነ ምግባር መርሆዎችን ማዘጋጀት እና ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

6/ To prepare and approve the necessary standard bidding documents, procurement list and catalog forms, manuals, and ethical principles to be followed by procurement and property administration professionals and heads, and to ensure their implementation;

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ መሠረት የተዘጋጁ መረጃዎች፣ እንዲሁም በግዥ አፈፃፀም እና በንብረት አወጋገድ ሂደት ጥፋት በመፈፀማቸው ለቢሮው በቀረቡ የጥፋተኝነት ሪፖርቶች ላይ የተሰጡ ውሣኔዎች፣ የአዲት ውጤቶች እና ሌሎች ሕዝብ ሊያውቃቸው የሚገባ ዋና ዋና ጉዳዮችን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት እና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለሕዝብ ይፋ ማድረግ፣

7/ To make public the information prepared in accordance with Sub-Article 6 of this Article, as well as the decisions made on the reports of misconduct submitted to the bureau for the implementation of procurement and property administration processes, audit results, and other important matters that the public should be aware of, using electronic systems and other means of communication as necessary;

፰/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መሥሪያ ቤቶች ካላቸው የሥራ ባህሪ በመነሳት ሊኖራቸው የሚገባውን የግዥና ንብረት አስተዳደር እና ተያያዥ ስራዎች አደረጃጀት አጥንቶ ማቅረብ፣ ተፈፃሚነቱን መከታተል፤

8/ To study and present, in collaboration with relevant bodies, the organization of procurement and property administration and related activities that the offices should have based on their work characteristics, and to monitor its implementation;

፱/ በመንግሥት ግዥ ወይም በሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጨረታ ለመሳተፍ ፍላጐት ያላቸው ተወዳዳሪዎች የሚመዘገቡበትን ዘመናዊ ሥርዓት መዘርጋትና ማስተዳደር፣

9/ To establish and manage a modern system for the registration of candidators interested in participating in public procurement or disposal of property,

፲/ የተቋም እና የሰው ኃይል አቅም ለማጎልበት የሚያስችል የአቅም ግንባታ እስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት እና የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት፣

10/ To prepare a strategic plan for capacity building to strengthen the capacity of the institution and human resources and to provide capacity building training,

፲፩/ ለመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር የሚያገለግል የመረጃ ቋት ማቋቋም፣ማጐልበት፣ መጠበቅ እና ወቅታዊነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ለመጠቀም እንደ አስፈላጊነቱ ተመጣጣኝ የክፍያ ተመን መወሰን፤

11/ Establish, develop, maintain and update a database for public procurement and property management, and determine appropriate fees for using the electronic system as necessary;

፲፪/ በክልሉ መንግስት እና በፌዴራል መካከል የተጣጣመ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ

12/ To ensure that there is a harmonized public procurement and property administration system between the regional government and the federal government,

፲፫/ የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር እንዲሁም የመንግሥት እና የግል አጋርነት ዘርፍ ግዥዎችን አፈፃፀም በራሱ ዕቅድ፣ እንዲሁም ጥፋት ስለመፈፀሙ ጥቆማ ሲቀርብለት ሂደቱን በማስቆም የሥርዓት መጠበቅ ወይም የግዥና ንብረት የክዋኔ ኦዲትና ክትትል የማካሄድ እና በግኝቱ መሠረት ተገቢውን እርምጃ እንደ አግባብነቱ በራሱ መውሰድ ወይም ሥልጣን ባላቸው ሌሎች አካላት እንዲወሰድ ማድረግ፣

13/ To maintain order by stopping the implementation of public procurement and property administration and public-private partnership sector procurements on its own initiative, and when a suggestion is made about the commission of a crime, to conduct performance audit and monitoring of the procurement and property operations and to take appropriate action on its own or to have other authorized bodies take action based on the findings, as appropriate;

፲፬/ የሚቀርቡ የጥፋተኝነት ሪፖርቶችን በማጣራት ጥፋት የተፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፫ መሠረት እንደጥፋቱ ክብደት ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግሥት ግዥ ወይም የመንግሥትን ንብረት በሽያጭ ለማስወገድ በሚወጣ ጨረታ እንዳይሳተፉ ማገድ፤

14/ To issue a warning according to the seriousness of the crime in accordance with Article 63 of this Proclamation when it confirms that a crime has been committed by examining the submitted crime reports, and to ban them from participating in public procurement or auctions for the sale of public property for a specific or indefinite period;

፲፭/ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራት ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን ተከትሎ መፈፀማቸውን መከታተልና መቆጣጠር፣ እንዲሁም ከመሥሪያ ቤቶች፣ ከአቅራቢዎች ወይም ከሕዝብ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መሠረት በማድረግ ምርመራ ማድረግና አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ፤ እንደሁኔታው የመውሰድ ሥልጣን ላለው አካል ማሳወቅ፤

15/ To monitor and control the implementation of public procurement and property administration activities in accordance with this Proclamation and the directives issued pursuant to this Proclamation, as well as to investigate and take administrative action based on complaints submitted by offices, suppliers or the public; to inform the competent authority as the case may be;

፲፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፭) ዓላማ፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብለትን አቤቱታ ለመፍታት እንዲችል ሰነዶች፣ መዛግብት፣ሪፖርቶች እና ማናቸውም ሌሎች ማስረጃዎች ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ከተወዳዳሪዎች፣ ከተጫራቾች ወይም ከአቅራቢዎች እና ከሌላ ማንኛውም ሰው እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣ እንዲሁም ምስክሮችን በመጥራት፣ ምስክሮችና ግዥው ወይም የሚወገደው ንብረት ሽያጭ የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመሐላ እንዲሰጡ ማድረግ፤

16/ For the purposes of sub-article (15) of this article, and also in accordance with article 59, sub-article (1) of this proclamation, to resolve claims submitted to it, can order the production of documents, records, reports and any other evidence from public bodies, candidates, bidders or suppliers and any other person, and to summon witnesses and to have the witnesses and the parties concerned in the acquisition or sale of the property to be disposed of swear their statements on oath.

፲፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፭) መሠረት በሚያደርገው ቁጥጥርና ምርመራ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ወይም ወንጀል እንዲታይ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ለሚመለከተው የሕግ አካል ማሳወቅ፣

17/ In the course of its supervision and investigation pursuant to Sub-Article (15) of this Article, when it believes that it is necessary to prosecute the matter in a civil or criminal manner, notify the relevant legal body;

፲፰/ እንደአስፈላጊነቱ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሙያተኞች ሊኖራቸው የሚገባውን ዕውቀትና ክህሎት መወሰን፣ የሙያ ብቃት የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሕግ ስልጣን ከተሰጣቸው ከሚመለከታቸው ተቋማት እንዲሰጣቸው የማድረግ፤

18/ To determine, in collaboration with relevant bodies as necessary, the knowledge and skills that professionals should possess, and to ensure that they are issued with professional qualification certificates from relevant institutions authorized by law;

፲፱/ አግባብነት ባለው የክልል መንግሥት አካል በክልሉ የመንግሥት ግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ላይ እንዳይሳተፍ የታገደ ተጫራች ወይም አቅራቢ በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ላይ እንዳይሳተፍ ለፌዴራል የመንግስት ግዥ እና ንብረት ባለስልጣን ማሳወቅ፤

19/ To notify the Federal public Procurement and Property Authority of any bidder or supplier who has been banned from participating in the procurement and disposal of public Property by the relevant regional government body, so that he may not participate in the procurement and disposal of public property by federal public bodies;

፳/ ለመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሙያ ዕድገት ከሚሰሩ እና በዘርፉ ለመሳተፍ ፍላጐት ካላቸው አካላት ጋር ተቋማዊ ግንኙነት በመፍጠር ተባብሮ መሥራት፣

20/ To establish institutional relations with entities that are working for the development of the public procurement and property administration profession and are interested in participating in the sector;

፳፩/ በክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር ያልሆነን የክልል መንግሥት ንብረት ወይም በሕግ ወይም ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ የክልል መንግሥት ንብረት እንዲሆን የተደረገን ማናቸውንም ንብረት በመንግሥት ንብረትነት የመያዝ፣ የማስተዳደር፣ በውሳኔ እንዲወገድ የማድረግ፣

21/ To hold, manage, and dispose of any property of the regional government that is not under the control of a regional public body or that has been declared the asset of the regional government by law or a decision issued by a competent court, as public property;

፳፪/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ጊዜያቸው ያለፈባቸው አደገኛ ኬሚካሎች ወይም የኬሚካል ውጤቶች፣ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ የኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች፣ መድኃኒቶች፣ ጨረር አመንጪ ዕቃዎች፣ የኢንዱስትሪ ዝቃጮችና የግብርና ተረፈ ምርቶች አያያዝና አጠባበቅ እንዲሁም አወጋገድ ላይ ጥናት በማከናወን የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ፤

22/ To conduct research and develop a system of procedures for the management, storage and disposal of expired hazardous chemicals or chemical products, obsolete electronic equipment, medicines, radioactive materials, industrial waste and agricultural by-products that may be harmful to health or the environment, in collaboration with relevant bodies;

፳፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት በክልሉ መንግስት የሚዘረጋውን ዘመናዊ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር የኤሌክትሮኒክ አሠራር ሥርዓት መቆጣጠር፣ ማስተዳደር፤

23/ To supervise and manage the modern procurement and property administration electronic system to be implemented by the regional government in accordance with this proclamation;

ክፍል አራት

መሠረታዊ የመንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ድንጋጌዎች

፲. የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ዕቅድ

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ መመሪያዎች ላይ የሚገለፁትን ዝርዝር ጉዳዮች ያካተተ ዓመታዊ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተዘጋጁት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ዕቅዶች በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ፀድቀው ለሚመለከታቸው የመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች እንዲሁም ዓመታዊ የግዥ ዕቅዱን በመመሪያው ላይ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ለቢሮዉ እና ለሕዝብ ይፋ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፲፩. የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሰነዶች ስለመያዝ

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከመንግሥት ግዥ እና የንብረት አስተዳደር ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ግዥው ከተፈፀመበት፣ ወይም ንብረቱ ከተወገደበት ቀን አንስቶ እስከ ፲ ዓመት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ይዘው ማቆየት አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ በተደነገገው መሠረት መሥሪያ ቤቶች የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራትን ኦዲት ለማድረግ ወይም ሌሎች በሕግ ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት በሚያመች ሁኔታ ሰነዶችን በተሟላ መልኩ አደራጅተው መያዝ አለባቸው፡፡

PART POUR

Basic Provisions on Public Procurement and Property Administration

10. Procurement and Property Administration Plan

1/ Public bodies shall prepare an annual procurement and property administration plan that includes the details specified in the directives issued pursuant to this Proclamation.

2/ The procurement and property administration plans prepared pursuant to sub-article (1) of this Article shall be approved by the head of the office and shall be made available to the relevant departments of the office and the annual procurement plan shall be made available to the bureau and the public electronically within the time limit specified in the directives.

11. Recording of Procurement and Property Administration documents

1/ Public bodies shall retain documents related to Public procurement and property administration in an electronic system for a period of 10 years from the date of the procurement or disposal of the property.

2/ In accordance with the provisions of Sub-Article 1 of this Article, public bodies shall organize and maintain documents in a manner that is convenient for auditing procurement and property administration activities or other legally authorized bodies.

ሸ/ ውል ከተፈረመ ወይም በማናቸውም ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ የግዥ አፈፃፀሙንና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳየውን መረጃ ተጫራቾች ሲጠይቁ እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አዋጅ፣ በአፈፃፀም መመሪያዎቹ ወይም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጐች ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት የለበትም፡-

ሀ) የመረጃው ይፋ መሆን በሕግ የማይፈቀድ፣ የሕግ አፈፃፀምን የሚያሰናክል፣ የሕዝብን ጥቅም የሚቃረን፣ የተዋዋዮችን ሕጋዊ የንግድ ጥቅም እንዲሁም ፍትሐዊ ውድድርን የሚጎዳ ከሆነ፣

ለ) ከተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሀሳብ ከመመርመርና ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ እና ተጫራቾች ያቀረቧቸውን የመጫረቻ ሰነዶች ይዘት የሚገልፁ መረጃዎች፣

3/ If a contract is signed or terminated for any reason, information showing the performance of the procurement and the details of the sale of the properties to be disposed of shall be made available to bidders upon request. However, unless ordered by this Proclamation, its implementing directives or other relevant laws, or by a court, public bodies shall not provide the following information:

A) If the disclosure of the information is prohibited by law, would impede the implementation of the law, would be contrary to the public interest, would be detrimental to the legitimate commercial interests of the bidders, or would be detrimental to fair competition;

B) Competitive proposal related to the examination and evaluation of the bids submitted by bidders and that describes the contents of the bidding proposals submitted by bidders;

፲፪. አድልዎ ያለማድረግ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዜግነት፣በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ሂደት በማንኛውም ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ላይ አድልዎ ማድረግ አይቻልም፡፡

12. Non-discrimination

Without prejudice to the provisions of Article 13 of this Proclamation, no discrimination shall be made against any candidates or bidder in the implementaion of public procurement and the sale of property to be disposed of on the basis of nationality, race or other grounds not related to the criteria for competition.

፲፫. ልዩ አስተያየት

፩/ ዝርዝር ሁኔታዎችና አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ በሚወሰነው መሠረት በጨረታ ግምገማ ወቅት ለሚከተሉት ልዩ አስተያየት ይደረጋል፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ለተመረቱ ዕቃዎች፣ በክልሉ ለሚገኙ አምራች ድርጅቶች እንዲሁም በመጠን፣ በአይነት፣ በጊዜና በዋጋ ተወዳዳሪ ምርት ወይም አገልግሎት ማቅረብ ለሚችሉ ለክልሉ ልማትም ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ አላቸው ብሎ ለለያቸው በክልሉ መንግስት ባለቤትነት ለሚተዳደሩ ድርጅቶች የሚበረታቱበትን ስርዓት ይዘረጋል፤

ለ) ለኢትዮጵያውያን ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ሰጪዎች፣ አማካሪያዎች እና ሥራ ተቋራጮች፣

ሐ) በውጭ ሀገር ድርጅቶችና በአገር በቀል ድርጅቶች መካከል ለሚመሠረት ጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የአሸሙር ማህበር፣ ወይም

መ) በማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት፣ አካል ጉዳተኞች፣ እና የነጋዴ ሴቶች ማህበራት እንዲሁም የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች፡፡

፪/ የስራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት ብቻ የሚሳተፉበት ግዥ እና ዝርዝር አፈፃፀም በዚህ አዋጅ መሠረት ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

13. Margin of Preference

1/ The following special considerations will be made during the evaluation of bids, as determined in the directive issued by the Bureau pursuant to this Proclamation, with specific conditions and implementation:

A) A system will be established to encourage products manufactured in Ethiopia, manufacturing organizations located in the region, and organizations owned and managed by the regional government that are considered to have high strategic importance for the development of the region and that can provide competitive products or services in terms of quantity, quality, time, and price.

B) Non-advisory service providers, consultants and contractors for Ethiopians;

C) For a partnership or joint venture between foreign organizations and local organizations, or

D) For micro and small enterprises engaged in production, associations of people with disabilities, and business women, as well as the results of technological innovation.

2/ Procurement and detailed implementation of which shall be limited to job creation institutions shall be determined by the directives to be issued by the bureau pursuant to this Proclamation.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቃዎች፣ ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች፣ የምክር አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ጥራትና ዋጋ ተመሳሳይ ሆኖ ተጫራቾች በግምገማ እኩል ነጥብ ሲያገኙ ለሀገር ውስጥ ምርቶች፣ ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች፣ የምክር አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) አፈፃፀም ማናቸውም ዕቃ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተመረተ ለመቆጠር ማሟላት ያለበት የአገር ውስጥ የታከለ እሴት ምጣኔ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈቀደውን ልዩ አስተያየት በጨረታ ሰነድ ውስጥ በግልፅ ማመልከት አለበት፡፡

፲፬. የግንኙነት ስልት

፩/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና በተወዳዳሪዎች፣ ተጫራቾች ወይም አቅራቢዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት በመጠቀም በጽሑፍ መደረግ አለባቸው፤

፪/ ቢሮው የመረጃ ልውውጡን ትክክለኛነት እና በሚስጥር መጠበቁን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን እና በቴክኒክ ረገድ ተፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግንኙነት ማድረግ የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

፲፭. ቋንቋ

፩/ ለብሔራዊ ጨረታ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ እና ጨረታው የሚካሄድበት ቋንቋ አማርኛ ይሆናል፡፡

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, where the quality and price of goods, non-consulting services, consulting services or construction works are the same, preference shall be given to domestic goods, non-consulting services, consulting services or construction works.

4/ For the purposes of sub-Article (1) letter (A) of this Article, the domestic value added rate that any goods must meet to be considered as manufactured in Ethiopia shall be determined by the directives issued pursuant to this Proclamation.

5/ The public body shall clearly indicate in the bidding document the special consideration permitted under Sub-Article (1) of this Article.

14. Mode of Communication

1/ Communications between public bodies and candidates, bidders or suppliers shall be in writing using electronic systems;

2/ The Bureau shall issue directives for electronic communication after ensuring that systems are in place to ensure the accuracy and confidentiality of information exchange and that the technical requirements are met.

15. Language

1/ The language of the bidding document prepared for the national bidding and the bidding process shall be Amharic.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ለግዥው ወይም ለሚወገደው ንብረት ሽያጭ አካሄድ አመቺና ፍትሐዊ ውድድርን የማይገድብ መሆኑ ሲታመንበት የጨረታ ሰነዱ የተወሰኑ ክፍሎች እና የመጫረቻ ሰነድ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲዘጋጅ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፫/ ለዓለም አቀፍ ግዥ ጨረታ ማስፈፀሚያ የሚዘጋጁት ማናቸውም ሰነዶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፲፮. የተወዳዳሪዎች ቅድመ ብቃት

፩/ በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግዥው ልዩ ባህርይ በመነሳት የሚያወጧቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ) የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የንግድ ግንኙነቶች ላለማድረግ ክልከላ ከጣለበት ሀገር የሚመጣ ዕቃና አገልግሎት አለመሆኑን፣

ለ) በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት ክልከላ ከተደረገባቸው ሀገራት ያልመጡ ዕቃዎችና ተዛማጅ አገልግሎቶች መሆናቸው ወይም ክፍያ እንዲፈፀምለት በምክር ቤቱ ክልከላ ያልተደረገበት ሰው ወይም ድርጅት፣

ሐ) በዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ እንዲሁም ሌሎች የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሕግ ሰነዶች በተገለፀው መሠረት የጥቅም ግጭት የሌለው፣

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this article, the public body may permit certain parts of the bidding proposals and the bidding document to be prepared in the English language, if it is satisfied that it is appropriate for the procurement or sale of the property to be disposed of and does not restrict fair competition.

3/ Any documents prepared for the implementation of an international procurement bid must be in the English language.

16. Pre-qualification of Candidates

1/ In order to participate in public procurement and sale of disposable property, candidates shall qualify by meeting the following criteria as appropriate, and such other criteria as the public body considers appropriate under the circumstances:

A) The goods and services are not imported from a country with which the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has imposed a ban on trade relations;

B) The goods and related services are not imported from countries that have been embargoed by the United Nations Security Council or the person or organization to whom the Council has not imposed a ban on payment;

C) Does not have a conflict of interest as defined in this Proclamation and the directives issued pursuant to this Proclamation and other documents on procurement and property administration;

መ) ውል ለመፈፀም የሚያስችል የሕግ ችሎታ ያለው፣

D) Has the legal capacity to enter into contracts;

ሠ) በዕዳ ያልተያዘ፣ ያልከሰረ ወይም የሥራ እንቅስቃሴውን ያላቋረጠ፣ ወይም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ያልታገደ፣

E) Is not in debt, bankrupt or has not ceased his business activities, or has not been suspended from business activities;

ረ) በመንግሥት ግዥ ወይም በሚወገደው ንብረት ሽያጭ እንዳይሳተፍ ታግዶ የነበረ ከሆነ የታገደበትን ጊዜ ያጠናቀቀ፣

F) If he has been suspended from participating in Public procurement or the sale of the property to be disposed of, he has completed the period of suspension;

ሰ) ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ቀደም ሲል በግዥ ፈፃሚው ወይም ንብረት አስወጋጁ መሥሪያ ቤት ሥር ሠራተኛ የነበረ እና የመጫረቻ ሰነድ ባቀረበበት ቀን መሥሪያ ቤቱን ከለቀቀ ከአንድ ዓመት በላይ የሆነው ሰው

G) A person who was previously an employee of the procurement or disposal office, the details of which are determined by the directives issued pursuant to this Proclamation, and who has left the office for more than one year on the date of submission of the bidding proposals;

ሸ) የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው እና በኢትዮጵያ የግብርና የታክስ ሕጐች በተደነገገው መሠረት የግብርና የታክስ ግዴታውን የተወጣ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴ የሌለው የውጭ ሀገር ድርጅት ከሆነ በተቋቋመበት አገር የተሰጠ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ እና የታደሰ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ፈቃዱን ወይም የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀቱን በሰጠው ሀገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በማረጋገጫ ያቀረበ፣ እና

H) A foreign company that has a renewed business license and has paid its agricultural tax obligations as prescribed by the Ethiopian Agricultural Tax Laws, and if it is a foreign company that does not have any commercial activities in Ethiopia, a valid business license and a renewed business registration certificate issued by the country where it was established, and a certificate of business registration certified by the Ethiopian Embassy in the country that issued the license or business registration certificate, and

ቀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴ የሌለው የውጭ ሀገር ድርጅት ካልሆነ በስተቀር የባንክ ሂሳብ ያለው፣

I) Has a bank account, except for a foreign organization with no business activity in Ethiopia,

፪/ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ማናቸውም በመንግሥት ግዥ ጨረታ ለመሳተፍ ፍላጐት ያላቸው ተወዳዳሪዎች የውድድር አቅማቸውንና ብቃታቸውን ለማሳደግ ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ አገር ድርጅት ጋር በእሽመር፣ በሽርክና ወይም በጊዜያዊ ህብረት/ጥምረት ማህበር በመደራጀት ለውድድር ሊቀርቡ ይችላሉ፤

2/ Unless otherwise specified in the bidding documents, any candidates interested in participating in a Public procurement bid may, in order to enhance their competitive capacity and competence, enter into a joint venture, partnership or temporary association with a local or foreign organization;

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ተወዳዳሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩት መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

3/ The Public body may require candidates to submit necessary documents to prove that they meet the requirements set forth in sub-article (1) of this article.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተወዳዳሪዎች እንዲሟሉ የሚጠበቁት መስፈርቶች በጨረታ ሰነድ ወይም የተጫራቾችን የመወዳደሪያ ሀሳብ ለመጠየቅ በሚዘጋጁ ሰነዶች ውስጥ መገለፅ አለባቸው፡፡

4/ The requirements expected to be met by candidates pursuant to sub-article (1) of this article shall be specified in the bidding documents or in the documents prepared for requesting candidates' proposals.

፭/ በመንግሥት የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ላይ ለመሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በጨረታው መሳተፍ ይችላል፡፡

5/ Any person who wishes to participate in the sale of property to be disposed of by the government may participate in the bid.

፮/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሀሰተኛ ማስረጃ ያቀረቡ ተጫራቾች ወይም ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ሲሉ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ወይም ያልተሟላ ማስረጃ ማቅረባቸው በማናቸውም ጊዜ የተረጋገጠባቸውን ተጫራቾች ከጨረታ ውድድር ውጪ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

6/ Public bodies shall disqualify any bidder who has submitted false documents or who has submitted any documents that are found to be fundamentally incorrect or incomplete in order to prove their qualifications.

፲፯. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

፩/ ስለግዥው ምንነት ትክክለኛና የተሟላ መግለጫ እንዲኖር እንዲሁም ተወዳዳሪዎች ፍትሐዊና ግልፅ በሆነ አሠራር መወዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚገዙትን ዕቃ፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት፣ የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ባህርይ የሚያሳይ የቴክኒክ ፍላጐት መግለጫ እንደ ግዥው ውስብስብነት ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመሆን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

፪/ የቴክኒክ ፍላጐት መግለጫው የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሊገዛ የሚፈልገውን ዕቃ ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ ጉዳት የማያደርስ መሆኑ እንደአስፈላጊነቱ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ወይም የአመራረቱን ሂደትና ዘዴ እንዲሁም ተፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሁኔታዎችን የሚያሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበት ሥርዓት የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

፫/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጐት መግለጫ እስከተቻለ ድረስ፡-

ሀ) በዲዛይን ወይም ባህሪያትን በመዘርዘር ላይ ሳይሆን በጠቀሜታ ላይ መሆኑን፣

ለ) ሀገራዊ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ደረጃውን ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ደረጃዎች ወይም የንግድ ቃላት ወይም የግንባታ ኮዶች መሠረት አድርጎ መዘጋጀቱን፣

ሐ) ሰፊ ውድድርን የሚጋብዝ እና ውድድርን ሊገድቡ የሚችሉ መግለጫዎች ያልተካተቱበት መሆኑን፣

17. Technical Spesification statement

1/ For the purpose of providing a correct and complete description of the object of procurement and facilitating fair and open competition between all candidates, Public body shall, in collaboration with the appropriate Public body depending on the complexity of the procurement, prepare, technical specifications and descriptions setting forth the characteristics of the goods, non-consultancy services, consultancy services or works to be procured.

2/ The technical requirements statement shall describe the system by which Public body shall ensure that the goods it seeks to purchase meet the quality, usefulness, non-harmfulness, as well as the measurement, identification, designation, packaging, or production process and method, as well as other required conditions.

3/ The technical requirements statement prepared by the Public body shall, to the extent possible:-

A) It's not about design or listing features, but about usability.

B) be based on a national standard or on internationally accepted standards or trade terms or building codes;

C) It should ensure that it does not contain any statements that invite wide competition and that they may restrict competition;

መ) ለሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና የሚያስፈልጉ መመዘኛዎችን ያካተተ መሆኑን፣ እና

ሠ) የሚገዛው ዕቃ፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ከባቢያዊ ብክለትን የማያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችሉ መመዘኛዎችን የያዘ መሆኑን፣ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ፍላጐት በትክክል ለመግለፅ አስቸጋሪ ካልሆነ ወይም ሌላ ዘዴ ከሌለ በስተቀር የቴክኒክ መግለጫው የተለየ የንግድ ምልክት ወይም ስም፣ ፓተንት፣ ዲዛይን ወይም የተወሰነን አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪን የሚጠቅስ መሆን የለበትም፡፡ ሆኖም አስገዳጅ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ ከላይ የተገለፁትን በማመልከት እና “ወይም ተመሳሳይ” የሚል ሐረግ በመጨመር የፍላጎት መግለጫውን ማዘጋጀት ይቻላል፡፡

፲፰. ጨረታን በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ስለማድረግ

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከሚከተሉት በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች የግዥ ወይም የንብረት ሽያጭ ውል ከመፈረሙ በፊት ጨረታን ወይም የመጫረቻ ሰነድን በማናቸውም ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ ይችላሉ፡-

ሀ) በግዥ አፈፃፀም እና ንብረት ሽያጭ ሂደት ላይ ውጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈፀሙ ከተረጋገጠ፣

D) It includes the criteria required for a life-cycle cost analysis; and

E) It must be ensured that the purchased goods, services or construction work, which are not subject to advice, meet the criteria to ensure that they do not cause environmental pollution.

4/ Unless it is difficult to accurately express the needs of the government office or there is no other way, the technical specifications should not refer to a specific trade mark or name, patent, design or a specific manufacturer or service provider. However, in cases of compelling circumstances, the specifications may be prepared by referring to the above and adding the phrase “or similar” as necessary.

18. Rejection of a Bid in Whole or Partially

1/ Public body may reject a bid or bidding proposal in whole or partially at any time before the signing of a purchase or sale contract for one or more of the following reasons:

A) If it is proven that an error has been made in the procurement and property sale process that may distort the results;

ለ) በሥራ ዕቅድ መቀየር ምክንያት ወይም የመሥሪያ ቤቱን ፍላጐት ለማሟላት ሌላ የተሻለ አማራጭ በመፈጠሩ ምክንያት ወይም ግዥውን ወይም የንብረት ሽያጩን ማካሄድ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ጥቅም የማያስገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ) የቀረቡት ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት የማያሟሉ ሲሆን፣

መ) በጨረታ የቀረበው ዝቅተኛ ዋጋ ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት ከሚያሰራጨው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ፣ ወይም ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት መረጃ ማግኘት የማይቻል ከሆነ እንደ ቅደም ተከተሉ ከታወቀ አምራች ዋጋ ወይም የገበያ ዋጋ ጥናት ለማድረግ ስልጣን በተሰጠው ተቋም ከሚገኘው ዋጋ አንፃር ከፍተኛ ልዩነት ያለው ሲሆን፣ ወይም የግንባታ ሥራ ግዥ ሲሆን የቀረበው ዋጋ እጅግ አነስተኛ ወይም የተጋነነ ዋጋ ሆኖ ሲገኝ፣ ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

ሠ) በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች የሰጠው ዋጋ የግዥ ፈፃሚ መሥሪያ ቤቱ ለግዥው ከያዘው በጀት በላይ ሲሆንና የበጀቱን ልዩነት ከሌላ ምንጭ ማሟላት የማይቻል ሲሆን ወይም ከሚሸጠው ንብረት የጨረታ መነሻ ዋጋ በታች ሲሆን፣

ረ) ተጫራቾች የግዥ ወይም የንብረት ሽያጭ ሂደቱን ለማዛባት በመመሳጠራቸው ወይም ሌሎች ከሥነ-ምግባር ውጪ የሆኑ ድርጊቶች በመፈፀማቸው ምክንያት በቂ ውድድር አለመደረጉ ሲረጋገጥ፡፡

B) Due to a change in the work plan or due to the emergence of another better option to meet the needs of the institution or when it is proven that the procurement or property sale does not provide economic or social benefits to the public body;

C) When the submitted bidders do not meet the minimum requirements set out in the bidding document;

D) The lowest price offered in the bid is significantly different from the current market price published by the Ethiopian Statistical Service, or if it is not possible to obtain information from the Ethiopian Statistical Service, from a known manufacturer's price or from a price obtained from an institution authorized to conduct market price research, respectively, or in the case of a construction project, the price offered is found to be extremely low or inflated, the details of which shall be determined by the directives issued by the Bureau.

E) The price offered by the winning bidder in the bid is higher than the budget allocated by the procurement office for the procurement and the budget difference cannot be met from other sources, or is lower than the starting price of the bid property,

F) When it is proven that there is insufficient competition due to bidders colluding to distort the procurement or sale process or engaging in other unethical practices.

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት ጨረታን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሲሠርዙ ምክንያቱን የሚገልፅ ማስታወቂያ ለተወዳዳሪዎች ወይም ለተጫራቾች ወዲያውኑ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

፫/ ጨረታውን ውድቅ የማድረግን ውሳኔ የተሰጠው ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ከሆነ የመጫረቻ ሰነዶቹ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ሚስጥራዊነቱ ተጠብቆ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጨረታን ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት ተጠያቂ አይሆኑም፡፡

፲፱. ዘመናዊ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ስለመዘርጋት

፩/ ቢሮዉ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሥርዓትን ወጪ ቆጣቢ፣ ግልጽ እና ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፣ መስሪያ ቤቶች እንዲተገብሩ ያደርጋል ሥርዓቱን በየጊዜው ያዘምናል፡፡፣

፪/ ቢሮዉ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ፡-

ሀ) የተዘረጋውን ኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለማዳበር እና ለማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶችን ያደርጋል፡፡

ለ) በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በተወዳዳሪዎች፣ በተጫራቾች፣ በአቅራቢዎች እና በተቆጣጣሪ አካላት የአሠራር ሥርዓቱን ለመተግበር የሚያስችል አቅም መፈጠሩን ያረጋግጣል፤

2/ When public bodies cancel a bid in whole or partially pursuant to sub-article (1) of this article, they shall immediately notify the candidates or bidders with a notice stating the reasons.

3/ If the decision to reject the bid is made before the bid is opened, the bidder proposals shall be kept confidential in an electronic system.

4/ Public bodies shall not be accountable for rejecting a bid in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

19. Establishing a modern procurement and Property Administration system

1/ The Bureau shall establish a modern electronic Public procurement and property administration system that will make the procurement and property administration system cost-effective, transparent and modern, and shall ensure that the offices implement and update the system regularly.

2/ The bureau shall, for the purposes of sub-article (1) of this Article:-

A) Conducts studies to develop and improve the electronic system implemented;

B) Ensures that the capacity of public bodies, candidates, bidders, suppliers and regulatory bodies to implement the system is created;

ሐ) የተዘረጋውን የኤሌክትሮኒክ አሰራር ሥርዓት ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፡

መ) በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ አጠቃቀም ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ የሳይበር ጥቃቶችን ለመከላከል ይህንኑ እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ጋር በትብብር ይሠራል፡፡

C) Monitors and manages the electronic system implemented;

D) Works in collaboration with the body authorized by law to manage the same to prevent cyber attacks that may occur during the use of the electronic system.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚዘረጋው የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት፡-

ሀ) የግዥ ዕቅድ ዝግጅትን፣

ለ) የጨረታ ማስታወቂያ አወጣጥን፣

ሐ) የማብራሪያ እና የማሻሻያ ጥያቄና ምላሽን፣

መ) የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብና አከፋፈትን፣

ሠ) የመጫረቻ ሰነድ ግምገማን፣

ረ) የይግባኝ ማጣራት ሥነ ሥርዓትን፣

ሰ) የውል አስተዳደርን፣

ሸ) በግዥና ንብረት አስተዳደር ሂደት የሚደረጉ የመረጃ ልውውጦችን እና

ቀ) እንደአስፈላጊነቱ ለዚህ ዓላማ ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ የሚገለጹ ሌሎች የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራትን ያካተተ ሊሆን ይገባዋል፡፡

3/ The electronic system established pursuant to sub-article (1) of this article shall include:

A) preparation of procurement plans,

B) issuance of bid notices,

C) requests for clarification and modification and their responses,

D) presentation and distribution of bidder proposal,

E) evaluation of bidder proposals,

F) appeals review procedures,

G) contract administration,

H) It should include information exchanges during the procurement and property process; and

I) Other procurement and property administration activities as specified in the directives issued by the bureau for this purpose, as necessary.

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ቢሮው ከወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው። ሆኖም የኤሌክትሮኒክ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ ሲፈጠር እና ቢሮው ሲያምንበት የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራትን ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ይከናወናል። ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

4/ Public bodies shall implement the modern electronic Public procurement and property administration system from the time the Bureau decides to implement it. However, when the implementation of the electronic procurement and property administration system is not possible and the Bureau believes it is necessary, the procurement and property administration activities shall be carried out through a non-electronic procurement and property administration system. The details shall be determined by the directives issued by the Bureau.

፭/ በዚህ አዋጅ እና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ የቀረበ ሰነድ ወይም የተደረገ ግንኙነት አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡

5/ Unless otherwise provided in this Proclamation and the directives issued by the Bureau, any document submitted or communication made in accordance with the system established in sub-article (1) of this Article shall be binding.

፳. ዘላቂነት ያለው የግዥና ንብረት አስተዳደርን ተፈፃሚ ስለማድረግ

20. Applying Sustainable Procurement and Property Administration

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንደ ግዥው ባህርይ ከአካባቢ ብክለት የፀዳ፣ መልሶ መጠቀምን የህይወት ዘመን ወጪ ትንተናን እና የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ከግምት ያስገባ ዘላቂነት ያለው የግዥ አፈፃፀም አሰራርን በፍላጎት መግለጫ፣ በመገምገሚያ መስፈርት፣ በውል ቃላትና ሐረጎች ዝግጅት ወቅት፣ እንዲሁም በውል አፈፃፀም ቁጥጥር ወቅት ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

1/ Public bodies shall implement a sustainable procurement implementation system that takes into account the nature of the procurement, free from environmental pollution, reuse, life cycle cost analysis, and community benefits, in the expression of interest, evaluation criteria, contract terms and clauses, and contract performance monitoring.

፪/ ዘላቂነት ያለው የግዥ አፈፃፀም ሥርዓት ዝርዝር አተገባበር በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ The detailed implementation of the sustainable procurement implementation system shall be determined by the directives issued pursuant to this Proclamation.

፳፩. የመንግሥት ግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሥነ-ምግባር

፩/ በግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ የተሰማሩ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚከተሉትን የሥነ-ምግባር መርሆዎች ተከትለው ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡፡

ሀ) የተፈጠረ ወይም ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭትን ማሳወቅ እና ራስን ከሂደቱ ማግለል፣

ለ) በተወዳዳሪዎች፣ በተጫራቾች እና በአቅራቢዎች መካከል አድልዎ አለማድረግ፣

ሐ) በሥራ አጋጣሚ ያወቃቸውን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን እና የተወዳዳሪዎችን፣ ተጫራቾችን ወይም የአቅራቢዎችን እንዲሁም የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ተጠቃሚዎችን መረጃ በሚስጥር መጠበቅ፣

መ) ከተወዳዳሪዎች፣ ከተጫራቾች ወይም ከአቅራቢዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መልኩ ስጦታ ወይም የሥራ ዕድል ወይም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት አለመቀበል፣

ሠ) በሥራ ሂደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሕግ አስፈፃሚ አካላት ማሳወቅ እና ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፣

ረ) ለመንግሥት ገንዘብ እና ንብረት ተቆርቋሪ መሆን፡፡

21. Ethics in Public Procurement and Property Administration

1/ Heads and employees engaged in procurement and property administration shall perform their duties in accordance with the following ethical principles:

A) To declare any existing or potential conflict of interest and to exclude themselves from the process,

B) Not to discriminate between candidators, bidders and suppliers,

C) To maintain the confidentiality of information acquired in the course of their work, including information about the public body, candidates, bidders or suppliers, and users of electronic systems,

D) Not to accept any gift or job opportunity or any thing or service of monetary value, directly or indirectly, from candidators, bidders or suppliers;

E) Report any suspected or actual acts of corruption to the relevant law enforcement bodies and assist in the fight against corruption and malpractice;

F) Be responsible for public funds and property.

፪/ ማንኛውም ተወዳዳሪ፣ ተጫራች ወይም አቅራቢ የመንግሥት የግዥ አፈፃፀምን እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭን ሊያዛቡ ከሚችሉ የሚከተሉት ተግባራት መቆጠብ አለበት፡-

ሀ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ተግባር ወይም ውሳኔ ለማዛባት ወይም ከግዥው አፈፃፀም እና ከሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ መሥሪያ ቤቱ ሊከተለው የሚገባውን አሠራር ለማስለወጥ በመደለያ መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ ከመስጠት ወይም ስጦታ ለመስጠት ቃል ከመግባት ወይም የሥራ ዕድል ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት ከመስጠት፤

ለ) የመንግሥት ግዥ አፈፃፀምን ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭን ለማዛባት በማሰብ የሀሰት ማስረጃ ከማቅረብ ወይም መገለፅ የነበረበትን መረጃ ከመደበቅ፤

ሐ) ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ከሌላ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሀሰት ውድድር ከማድረግ፣

መ) በመንግሥት ግዥ ወይም በሚወገድ ንብረት ሽያጭ ሂደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈፃሚ አካላት ካለማሳወቅ እና ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት ካለማገዝ፡፡

2/ Any candidates, bidder or supplier shall refrain from the following acts that may distort the execution of public procurement and the sale of properties to be disposed of:

A) Giving or promising to give any gift or employment opportunity or any other thing or service of monetary value, directly or indirectly, in order to influence the actions or decisions of a government official or employee or to change the procedures to be followed by the office in connection with the execution of the procurement or the sale of the property to be disposed of;

B) Providing false evidence or concealing information that should have been disclosed with the intention of distorting the execution of the public procurement or the sale of the property to be disposed of;

C) Collusion with another candidator with the intention of obtaining an improper advantage,

D) Failure to report to law enforcing bodies any suspected or actual corruption in public procurement or disposal of properties and to assist in the fight against corruption and malpractice.

ክፍል አምስት

የግዥ ዘዴዎችና ስልቶች

፳፪. የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች

፩/ በማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ግዥ አፈፃፀም የሚከተሉት የግዥ ዘዴዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፡-

ሀ) ግልፅ ጨረታ፣

ለ) በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ፣

ሐ) ውስን ጨረታ፣

መ) በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ፡፡

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተዘረዘሩት ውስጥ ለእያንዳንዱ ግዥ ተገቢ የሆነውንና ለመንግሥት ገንዘብ ከፍተኛ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችለውን የግዥ ዘዴ በመምረጥ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አግባብነት ያለውን የግዥ ዘዴ ሲጠቀሙ በሥራ ላይ እንዲውል የተመረጠው የግዥ ዘዴ ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟላ መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

፬/ የሚፈፀመው ግዥ ከአንድ በላይ የሆኑ የግዥ ዓይነቶችን አጣምሮ የያዘ ሲሆን ግዥው ከአጠቃላይ የግምት ዋጋ ቢያንስ ከ፶ (ሃምሳ) በመቶ በላይ የሆነውን የግዥ ዓይነት ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

PART FIVE

METHODS AND APPROACHES OF PROCUREMENT

22. Authorized Methods of Procurement

1/ The following procurement methods shall be used in the implementation of any procurement by public bodies:

A) Open bid,

B) Selective tender,

C) Limited tendering,

D) Direct procurement.

2/ Public bodies shall select and implement the procurement method that is appropriate for each procurement and that will provide the greatest benefit to public funds from among those listed in sub-article (1) of this article.

3/ When using the appropriate procurement method in accordance with sub-article (2) of this article, public bodies shall maintain a document stating that the selected procurement method meets the necessary pre-conditions for its implementation.

4/ The procurement to be carried out shall consist of a combination of more than one type of procurement and the procurement shall be carried out following the procurement method that is at least 50 percent (fifty) of the total estimated value.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ቢኖርም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ የተዘረጋውን ሥርዓት ጠብቀው ግዥ መፈፀም የማይችሉበት ሁኔታ ሲያጋጥም ግዥውን በልዩ ሁኔታ መፈፀም የሚችሉበት የአሠራር ሥርዓት በተመለከተ ቢሮዉ መመሪያ ያወጣል፡፡

፳፫. ግልፅ ጨረታ

፩/ ግልፅ ጨረታ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፍላጎት ላላቸው ሁሉም ተጫራቾች እኩል ዕድል በሚሰጥ ጨረታ ግዥ የሚፈፅምበት ዘዴ ሲሆን፣ በግልፅ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በቢሮዉ የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና በዚህ አዋጅ ክፍል 7 እና በአዋጁ መሠረት በሚወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ የተመለከተውን የጨረታ ሥርዓት ተከትሎ መከናወን አለበት፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም ያላባቸው ሲሆን ግልፅ ጨረታን ለማስቀረት በማሰብ በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች መክፋፈል የለባቸውም፡፡

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ ሌሎች የግዥ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በሚወጣው መመሪያ የተገለፁትን አሠራሮች ግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ የግዥ ዘዴው በግዥ ዕቅድ ውስጥ መካተት አለበት፡፡

5/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this article, in cases where public bodies are unable to carry out procurement in accordance with the system established by this proclamation, the Bureau shall issue directives regarding the procedure for carrying out the procurement under special circumstances.

23. Open Bid

1/ Open bidding is a method of procurement by public bodies that provides equal opportunity to all interested bidders. Procurement through open bid shall be carried out in accordance with the standard bidding document prepared by the bureau and the bidding process specified in part 7 of this Proclamation and the Procurement Implementation directives to be issued pursuant to the Proclamation.

2/ Except as permitted by this Proclamation, public bodies shall not conduct any procurement through open bid and shall not divide procurements that should be conducted together with the intention of avoiding open bid.

3/ When public bodies use procurement methods other than open bid, the procurement method must be included in the procurement plan, taking into account the procedures specified in the directives issued for the implementation of this proclamation.

፳፬. በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ

፩/ በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ የግዥ ዘዴ በጨረታ መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾችን ከአንድ ደረጃ በላይ በሆነ ውድድር በማጣራት እና በመጀመሪያው ደረጃ ያለፉ ተጫራቾችን ለቀጣይ ዙር ውድድር በመጋበዝ ከተጫራቾች መካከል የጨረታው አሸናፊ የሚመረጥበት የግዥ ዘዴ ሲሆን፣ የሁለት ደረጃ ጨረታ፣ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ወይም የፍላጎት መጠየቂያ ጨረታን ያካትታል፡፡

፪/ የሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ ውስብስብ ለሆኑና ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ መሥሪያ ቤቶች ሁለት ዙር ጨረታ በማውጣት ፍላጎታቸውን ሊያሟላ የሚችል የመጫረቻ ሰነድ ያቀረበን ተጫራች በአሸናፊነት የሚመርጡበት ሥርዓት ሲሆን ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ መሟላቱ መረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) ለሚፈለገው ግዥ በመሥሪያ ቤቱ ደረጃ የተሟላ ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም የግዥውን ባህሪ ለይቶ ለማሳየት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እና የመሥሪያ ቤቱን የግዥ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል መፍትሄ ሲፈለግ፣

ለ) ግዥው የሚካሄደው በገበያ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ለማምረት ወይም የምርምር እና የልማት ወጪዎችን ለመተካት ሳይሆን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የምርምር፣ የሙከራ፣ የጥናት እና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ውል መፈፀም ሲፈልግ

24. Selective Tendering

1/ Selective tendering is a procurement method in which the winner of the bid is selected from among the bidders by screening the bidders who wish to participate in the bid in more than one stage of selective and inviting the bidders who have passed the first stage to the next stage of selective. It includes two-stage bidding, a pre-qualification bidding or a request for proposals bidding.

2/ Two-stage bidding is a system in which the offices conduct two rounds of bidding for complex procurements and select the bidder who has submitted a bidding proposal that meets their needs, provided that one of the following conditions is met: -

A) When it is impossible to prepare a complete detailed statement of requirements for the required procurement at the office level or when it is impossible to clearly identify the nature of the procurement and when a solution is needed to meet the office's procurement needs to a high level;

B) The procurement is not for the production of marketable goods or to replace research and development costs, but when public body seeks to enter into a contract to carry out research, testing, study and development activities;

ሐ) ጨረታ እንዲወጣ ተደርጐ በሚፈለገው ግዥ ባህርይ ወይም ተፈጥሮ ግልፅ አለመሆን ምክንያት ተወዳዳሪዎች በጨረታው ያልቀረቡ እንደሆነ ወይም የቀረቡት የመጫረቻ ሰነዶች ውድቅ ሲደረጉ እና ይህም የሆነው መሥሪያ ቤቱ የተሟላ የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር ማዘጋጀት ባለመቻሉ መሆኑ ሲታመን፣

መ) የሚገዛውን ዕቃ፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት፣ የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ባህርይ ወይም ተፈጥሮ አስመልክቶ ከተወዳዳሪዎች ጋር ውይይት ማድረግ ሲያስፈልግ፡፡

C) Where a bid has been issued and the characterstics or nature of the procurement is unclear, no bidders have submitted their bids or the bidders proposals submitted have been rejected, and it is believed that this was due to the inability of the office to prepare a complete list of requirements;

D) When it is necessary to discuss with candidates the nature or character of the goods, non-consulting services, consultancy services or construction work to be purchased.

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዥው ከሚኖረው የተለየ ባህርይ አንፃር በቅድሚያ የተወዳዳሪዎችን ብቃት መሠረት በማድረግ ግምገማ ማድረግ አለብኝ ብሎ ሲያምኑ እንደግዥው ዓይነት ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ በማውጣት ግዥ ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡

3/ When public bodies believe that they need to conduct a preliminary evaluation of the qualifications of the candidates due to the specific nature of the procurement, they may conduct procurement by issuing a national or international pre-qualification bid, depending on the type of procurement.

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የምክር እና ሌሎች አዕምሯዊ የሙያ አገልግሎት ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንደ ሁኔታው ተወዳዳሪዎች የፍላጎት መግለጫ ወይም የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ በማድረግ የተሻለ ብቃት ያለውን አማካሪ ድርጅት በመምረጥ ግዥ የሚፈፅሙበት አሠራር በመመሪያ ይወሰናል፡፡

4/ The procedure for conducting procurement by public bodies for the provision of consulting and other intellectual professional services to the best qualified consulting firm shall be determined by the directive, by inviting candidates to submit expressions of interest or competitive proposals, as the case may be.

፳፭. ውስን ጨረታ

25. Limited Tendering

፩/ የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት ሳያስፈልግ ቁጥራቸው ውስን ለሆኑ ተሳታፊዎች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት አድራሻቸው በሚላክ ግብዣ መሠረት የሚቀርቡ ተጫራቾችን በማወዳደር የጨረታው አሸናፊ የሚመረጥበት የግዥ ዘዴ ነው፡፡

1/ Limited tendering is a procurement method in which a limited number of participants are invited to submit their bids electronically, without the need to issue a bid notice, and the winner of the bid is selected by comparing the bidders who submit their bids based on an invitation sent to their addresses.

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲሟሉ ለተገደበ ጨረታ ወይም በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ የተመለከቱ አሠራሮችን በመከተል ግዥ ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡

፫/ የተገደበ ጨረታ በቁጥር በተገደቡ ተጫራቾች መካከል ውድድር በማካሄድ የግልፅ ጨረታ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሥርዓት የሚፈፀም ግዥ ሲሆን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተገደበ ጨረታ ግዥ መፈፀም የሚችሉት ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ሲሟላ ይሆናል፡፡-

ሀ) ለመግዛት የተፈለገው ዕቃ፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት፣ የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ከተወሰኑ ድርጅቶች ብቻ የሚገኝ መሆኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ በሚቀመጥ ሥርዓት ሲረጋገጥ፣

ለ) የግዥው መጠን ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ለተገደበ ጨረታ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን፣ ወይም

ሐ) የተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ በማይገድብ ሁኔታ የተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ በመጠቀም ቢያንስ አንድ ጊዜ ግልፅ ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪ ወይም የመሥሪያ ቤቱን ፍላጎት የሚያሟላ ተጫራች ያልተገኘ ሲሆን፣

፬/ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ እስከተቻለ ድረስ ከሦስት ያላነሱ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ውሳኔ ለሁሉም ተወዳዳሪዎች ክፍት በማድረግ በሚሰበሰብ የዋጋ ማቅረቢያ ውድድር አሸናፊው ተጫራች የሚመረጥበት ሥርዓት ሲሆን ከዚህ በታች የተቀመጡ ድንጋጌዎች ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

2/ Public bodies may conduct procurement by following the procedures specified for limited tendering or competitive bidding when the conditions set forth in sub-articles (3) and (4) of this article are met.

3/ A bid is a procurement carried out in a manner similar to an open bid by conducting competition among a limited number of bidders. Public bodies may conduct procurement through a bid when one of the following conditions is met:

A) When it is confirmed through a system established by the Bureau in accordance with this Proclamation that the goods, non-consulting services, consulting services or construction work to be purchased are available only from certain organizations;

B) The amount of the procurement does not exceed the amount set for a limited bid in the directives issued by the bureau, or

C) At least one open bid has been issued using a bidder document prepared in a manner that does not restrict the participation of candidates and no candidates or bidder meeting the needs of the Office has been found,

4/ A procurement conducted through a bidding process shall be conducted by inviting, as far as possible, not less than three bidders or by decision of the public body, making it open to all candidators, and the winning bidder shall be selected in accordance with the provisions set forth below.

ሀ) ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት ለዚህ የግዥ ዘዴ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ እና የሚገዙት ዕቃዎች ለገበያ ተብለው የተዘጋጁ፣ ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ወይም የታወቀ ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች፣ ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች፣ የምክር አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ሥራዎች ሲሆኑ ነው፡፡

A) Unless otherwise provided in a directive issued by the Bureau, public bodies may make procurements through price bidding for items that do not exceed the amount authorized for this procurement method and are intended for sale, are not immediately available for use or cannot be purchased in bulk, or are of known value, non-consulting services, consulting services, or construction works.

ለ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም በክልሉ መንግሥት ሥር ያሉ የትምህርት ተቋማት የምግብ ግብዓት አቅርቦቶችን እና ሸቀጣ ሸቀጦችን በማምረት ዘርፍ ከተሠማሩ ህብረት ስራ ማህበራት ወይም ከአምራቾች ወይም ከአስመጪዎች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የሚፈፅሙበት የተለየ አሠራር በዚህ አዋጅ መሠረት ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

B) Notwithstanding the provisions of letter (A) of this sub-article, the specific procedure for educational institutions under the regional government to purchase food supplies and commodities from cooperatives engaged in the production sector or from manufacturers or importers at a competitive price shall be determined by the directives issued by the Bureau pursuant to this Proclamation.

ሐ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ባላቸው የተለየ የሥራ ባህሪ ምክንያት የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ወይም ሌሎች ተመሳሳይ አማራጮችን በመጠቀም ለጥናት እና ምርምር፣ እንዲሁም ለሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ግብዓቶችን፣ የቆይታ ጊዜያቸው አጭር የሆኑ ዕቃዎችን ወይም ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ ሊፈፀሙ የሚገባቸው ግዥዎችን በዋጋ ማቅረቢያ ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡

C) Notwithstanding the provisions of letter (A) of this sub-article, public bodies may, due to the specific nature of their work, use electronic procurement systems or other similar options to make purchases on a competitive basis for inputs that may be used for study and research, as well as medical equipment, items with a short shelf life, or purchases that must be made confidentially.

መ) በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ውስጥ መካተት አለበት፡፡

ሠ) አስገዳጅ ሁኔታ በማጋጠሙ ምክንያት ከዕቅድ ውጪ የሚፈፀም የዋጋ ማቅረቢያ ግዥ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ መፈቀድ ይኖርበታል፡፡

ረ) በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ አማራጭ ተወዳዳሪዎች እስካለ ድረስ በተደጋጋሚ የተወሰኑ ተወዳዳሪዎችን ብቻ በመጋበዝ ማወዳደር አይቻልም፡፡ በመሆኑም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እስከተቻለ ድረስ በዘርፉ ለተሠማሩ ሌሎች ተወዳዳሪዎች ተመጣጣኝ የመወዳደር ዕድል መሰጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፳፮. በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ

፩/ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዥን በቀጥታ መፈፀም የሚችሉት ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲሟላ ሲሆን፣ ይህ የግዥ ዘዴ በአቅራቢዎች ወይም ተወዳዳሪዎች መካከል ውድድር እንዳይኖር ወይም አንድን ተጫራች ለመጥቀም ታስቦ ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ሀ) ዕቃው፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎቱ፣ የምክር አገልግሎቱ ወይም የግንባታ ሥራው የሚገኘው ከአንድ ተወዳዳሪ ብቻ ሲሆን፣

D) Procurement through bids must be included in the annual procurement plan of public bodies.

E) Procurement through bids that are not planned due to exigent circumstances must be approved by the head of the public body.

F) For a procurement conducted through price bidding, it is not possible to repeatedly invite only certain candidators to compete, as long as there are alternative competitors. Therefore, the government office must ensure that, to the extent possible, other candidators engaged in the sector are given a fair opportunity to compete.

26. Direct Procurement

1/ The detailed implementation of which shall be determined by the directives issued by the Bureau, public bodies may directly procure when one of the following conditions is met, and they shall be responsible for ensuring that this procurement method is not used to prevent competition between suppliers or candidate s or to benefit a single bidder.

A) The goods, services other than consultancy, consultancy services or construction works are available from only one candidate;

ለ) ግዥው በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ወዲያውኑ ካልተፈፀመ በሰው ሕይወት እና ንብረት ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥርና በመሥሪያ ቤቱ ሥራ አፈፃፀም ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

B) The procurement is so urgent that if not carried out immediately, it will cause serious harm to human life and property and will cause damage to the performance of the work of the office;

ሐ) መሥሪያ ቤቱ ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ችግር ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የሚፈለገው አቅርቦት በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ማሳካት ያልተቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

C) The required supply cannot be achieved by other procurement methods, except for a problem with the bidding documents prepared by the office;

መ) አስቀድሞ ለተገዙ ዕቃዎች ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ተጓዳኝ ወይም መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን መግዛት ሲያስፈልግ እና እነዚህን ተጓዳኝ ወይም መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን ከሌላ ተወዳዳሪ መግዛት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከሚጠቀምበት ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ምክንያት ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት የግድ ሲሆን፣

D) When it is necessary to purchase ancillary or replacement goods or additional services for previously purchased goods or services other than those provided by the government office, and it is necessary to purchase these ancillary or replacement goods or additional services from another candidator because they are incompatible with the goods or services used by public body,

ሠ) በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በመጀመሪያ ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ማሠራት አስፈላጊ ሲሆንና በቴክኒክ ወይም በኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ምክንያት እነዚህን ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ከመጀመሪያው ውል ነጥሎ ማሠራት የማይቻል ሲሆን፣

E) Without prejudice to the limitations set out in the procurement directives, where, due to unforeseen circumstances, it is necessary to carry out additional construction works not included in the original contract and it is not possible to carry out these additional construction works separately from the original contract due to technical or economic reasons;

ረ) በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አሸናፊው በውድድር ከተመረጠ በኋላ በተፈረመ ውል ውጭ የመጀመሪያው ግዥ የተከናወነባቸው ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ሥራዎች ወይም አቅርቦቶች ውል አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ መጠናቀቁ እና ቁጠባንና ቅልጥፍናን የሚያስገኝ መሆኑ በመረጋገጡ ቀደም ሲል ውሉን ከፈረመው አቅራቢ እንዲሠራ ወይም እንዲቀርብ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን፣

F) Without prejudice to the limitations set out in the procurement directives, where it is necessary to procure from the supplier who previously signed the contract, a non-consulting service or consultancy work or supply for which the first procurement was made after the winner has been selected through competition, provided that the contract has been satisfactorily completed and that it provides savings and efficiency,

ሰ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚኖራቸው የተለየ የግዥ ፍላጎት ማሟያ ከገበያ በለቀማ ግዥ መፈፀም የሚያስገድዳቸው ሁኔታ ሲፈጠር፣ ወይም በግዥ መመሪያው ከሚወሰን የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ጥቃቅን ግዥዎች ሲሆኑ፣

G) When a situation arises that requires public bodies to make purchases from the market to meet their specific procurement needs, or when they are small purchases that do not exceed the amount determined by the procurement directives,

ሸ) ሽያጩ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ፣ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ የሚፈፀም እና በመደበኛ አቅራቢነት ከተሰማሩ ተወዳዳሪዎች ሊገኝ የማይችል ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ሲሆን፣

H) When the sale is for a short period of time, is made in a way that provides special benefits to the public body, and is a purchase of goods or services that cannot be obtained from candidates engaged in regular supply,

ቀ) የመንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ለሚኖራቸው የዕቃና አገልግሎት ግዥ ፍላጎት ወጪን በመሸፈን ከመንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤት ግዥ መፈፀም ሲያስፈልግ፣

I) When it is necessary to make a purchase from a public budget body to cover the cost of purchasing goods and services of government budget offices;

በ) መሥሪያ ቤቶች ባላቸው የተለየ የሥራ ባህርይ ምክንያት በውድድር ሊገኙ የማይችሉ ለጥናት እና ምርምር፣ ለሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን እንዲሁም ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ ሊፈፀሙ የሚገባቸው ግዥዎችን ሌላ የተለየ አማራጭ ባለመኖሩ ምክንያት ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ግዥ መፈፀም አስፈላጊ መሆኑ በበላይ ኃላፊው ሲታመንበት፤

J) When top of the head believes that it is necessary to make a direct purchase from a single supplier due to the lack of other alternatives for procurement of resources for research and medical equipment, which cannot be obtained through competition due to the specific nature of the work of the offices, as well as procurements that must be carried out in a confidential manner;

ተ) በሌላ ግዥ ፈፃሚ መሥሪያ ቤት ቀደም ሲል በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ ከተገዙ ዕቃዎች ወይም ከምክር ውጭ ከሆኑ አገልግሎቶች ጋር በዓይነት እና በዋጋ አንድ ዓይነት የሆነ ግዥዎችን ቀደም ሲል አቅርቦቱን ከፈፀመው አቅራቢ ለአንድ ጊዜ ብቻ መፈፀም ከጊዜ እንዲሁም ለመሥሪያ ቤቱ ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አንፃር አዋጭ መሆኑ በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሲታመንበት፣

K) When the head of the office is believed that it is feasible, in terms of time and economic benefit to the office, to make purchases of goods and services that are identical in type and price to those previously purchased through an open bid procedure by another procuring office or services that are not subject to consultation, only once from the supplier that previously made the supply;

ቸ) ዋጋቸው በመንግሥት የሚወሰን ዕቃዎች እና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ሲሆኑ፣

L) When the price of goods and services that are not subject to consultation is determined by the government;

ኘ) ዕቃው ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎቱ ወይም የምክር አገልግሎት በሚታወቁ እና ቢሮዉ በየጊዜው በሚለየው የድርጅቶች ዝርዝር ውስጥ በተካተቱ ድርጅቶች በበይነ-መረብ ገበያ የሚገኝ፣ ዋጋው አስቀድሞ በበይነ መረብ ለሕዝብ ይፋ የተደረገ፣ ግዥው በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ብቻ የሚፈፀም እና የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በዚህ መልኩ ግዥው መፈፀሙ የመንግሥትን እና የመሥሪያ ቤቱን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ሲያምንበት፡፡

M) The goods, services or consultancy services are available on the Internet market from organizations known and included in the list of organizations that the Bureau periodically determines, the price is previously announced to the public on the Internet, the procurement is carried out exclusively by electronic means, and the head of the Office believes that the procurement in this manner is in the interests of the government and the Office.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሰ) እና (ኘ) መሠረት በቀጥታ ለሚፈፀሙ ግዥዎች የፅሑፍ ውል መዋዋል አያስፈልግም፡፡

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት የሚፈፅሟቸውን ግዥዎች በሌሎች ዘዴዎች መፈፀም የማይቻል መሆኑን የሚያረጋግጥ፣ እንዲሁም ግዥውን ከአንድ አቅራቢ ለመፈጸም ያስፈለገበትን አሳማኝ ምክንያት፣ተፈላጊ ጥራት፣ብዛት፣የማቅረቢያ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያስረዳ በሰነድ የተደገፈ መግለጫ መያዝ አለባቸው፡፡

፬/ ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ በሚፈፀም ግዥ ድርድር የሚደረግባቸው ሁኔታዎች እና ዝርዝር ሂደት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፳፯. የገበያ አማራጮች

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከሚፈፅሙት ግዥ ዓይነት፣ ባህሪ እና የገንዘብ መጠን በመነሳት ብሔራዊ ወይም ዓለም ዓቀፍ የገበያ አማራጭን በመጠቀም ግዥ ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ሌሎችን የገበያ አማራጮች ሊወስን ይችላል።

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የገበያ አማራጭ ግዥ ለመፈፀም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤

ሀ) የግዥው ግምታዊ ዋጋ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ከተፈቀደው የገንዘብ ጣሪያ በታች መሆኑን፣ ወይም

2/ A written contract shall not be required for direct procurements pursuant to sub-article (1) letter (g) and (O) of this Article.

3/ Public bodies shall maintain a documented statement confirming that the procurements they undertake pursuant to the provisions of this Article cannot be carried out by other means, and shall provide a compelling reason for the need to procure from a single supplier, as well as the required quality, quantity, delivery time and conditions.

4/ The conditions and detailed process for negotiating procurement directly from a single supplier shall be determined by directive.

27. Market Options

1/ Public bodies may make purchases using national or international market options, depending on the type, nature and amount of the procurement. The Bureau may, if necessary, determine other market options through directives issued by the Bureau.

2/ Public bodies must ensure that the following conditions are met in order to conduct market alternative procurement through a national open bid:

A) The estimated value of the procurement is below the threshold for international open bid as set out in the Procurement Implementation Directives to be issued pursuant to this Proclamation, or

ለ)የግዥው ግምታዊ ዋጋ በግዥ አፈፃፀም መመሪያው ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ከሚወሰነው የገንዘብ ጣሪያ በላይ ቢሆንም፣ የሚፈለገውን አቅርቦት ማግኘት የሚቻለው በሀገር ውስጥ ብቻ መሆኑን፣

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የገበያ አማራጭ ግዥ ለመፈፀም ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ መሟላቱን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤

ሀ) የግዥው ግምታዊ ዋጋ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ከተመለከተው የገንዘብ ጣሪያ በላይ መሆኑን፣ ወይም

ለ)የግዥው ግምታዊ ዋጋ በግዥ አፈፃፀም መመሪያው ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ከሚወሰነው የገንዘብ ጣሪያ በታች ቢሆንም፣ የሚፈለገውን ግዥ በሀገር ውስጥ መፈፀም የማይቻል መሆኑን፣

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውጪ ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ካልተደረገ በስተቀር ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይቻል ሲታመንበት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጪ ሌሎች የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም በብሔራዊ ወይም በዓለም አቀፍ የገበያ አማራጮች ግዥ መፈፀም ይችላሉ፡፡

፭/ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተገለፀው መሠረት ሌሎች የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም ከዓለም አቀፍ ገበያ ግዥ መፈፀም የሚቻለው በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው መመሪያ ለየግዥ ዘዴዎች የተቀመጠውን አሠራር ተከትሎ መሆን አለበት፡፡

B) Eventhough the estimated value of the procurement is above the threshold for national open bid as set out in the Procurement Implementation Directives, but the required supply can only be obtained domestically;

3/ Public bodies must ensure that one of the following conditions is met in order to conduct market option procurement through international open bid:

A) The estimated value of the procurement exceeds the threshold for national open bid as set out in the directives to be issued pursuant to this Proclamation, or

B) The estimated value of the procurement is below the threshold for international open bid as set out in the directives for procurement, but the required procurement cannot be carried out domestically;

4/ Without prejudice to the provisions of sub-articles 2 and 3 of this article, where it is believed that effective competition cannot be achieved without the participation of foreign companies, government offices may make purchases through national or international market options using other permitted procurement methods other than open bid.

5/ Unless otherwise provided for in this Proclamation and the directives to be issued by the Bureau pursuant to this Proclamation, procurement from the international market using other procurement methods as described in Sub-Article (4) of this Article shall be carried out in accordance with the procedures set out for the different procurement methods in this Proclamation and the directives to be issued pursuant to this Proclamation.

፮/ ቢሮው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዓለም አቀፍ ጨረታ ወቅት ሊጠቀሙ የሚገባቸውን ዓለም አቀፍ የንግድ ቃላትና ሁኔታዎች ይወስናል፡፡

፳፰. የግዥ ስልቶች

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንደ ግዥ ባህሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስልቶች በመጠቀም ግዥ መፈፀም ይችላሉ፡፡

ሀ) ስትራቴጂያዊ ግዥ፣

ለ) በማዕቀፍ የሚፈፀም ግዥ፣

ሐ) የጋራ ግዥ፣

መ) በሊዝ ስምምነት የሚፈፀም ግዥ፣

ሠ) በራስ ኃይል የሚፈፀሙ ሥራዎች ግዥ፣

ረ) የተርንኪ ግዥ፣

ሰ) የኤሌክትሮኒክ ልዉውጥ ሐራጅ ጨረታ፡፡

፪/ ክልላዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆናቸው በማዕከል የሚፈፀሙ ስትራቴጂያዊ ግዥዎች በቢሮዉ የሚወሰኑ ሲሆን ግዥውም በቢሮው ይፈፀማል፡፡

፫/ የማዕቀፍ ግዥ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተከታታይነት ያላቸው የተናጠል ፍላጎቶቻቸው ለማሟላት ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ መሥሪያ ቤቶች በተከታታይ የሚፈለጉ ተመሳሳይነት ያላቸው ዕቃዎችና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ግዥ በጥቅል በማዕከል የሚፈጸምበት የግዥ ስልት ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ እና አንቀጽ ፶፪ ላይ የተደነገገውን አሠራር ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

6/ The Bureau shall determine the international commercial terms and conditions that Public body shall use during international bidding.

28. Procurement Approach

1/ Public bodies may conduct procurement using the methods listed below, depending on the nature of the procurement.

A) Strategic Procurement,

B) Framework Procurement,

C) Joint Procurement,

D) Lease Procurement,

E) Own force Procurement,

F) Turnkey Procurement,

G) Electronic Reverse Auction.

2/ Strategic procurements to be carried out centrally, as they are of regional importance, shall be decided by the bureau and the procurement shall be carried out by the bureau.

3/ Framework procurement is a procurement method whereby public bodies, in order to meet their successive individual needs or to procure similar goods and non-consultant services required by more than one offices, are centrally implemented in a single package, and is carried out in accordance with the procedures stipulated in Articles 51 and 52 of this Proclamation.

፬/ የጋራ ግዥ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ መሥሪያ ቤቶች ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በሚያወጣው ዝርዝር ያልተካተቱና የጋራ ፍላጎታቸውን ለማሟላት በሚወጣ ጨረታ መሠረት አሸናፊ ከሚሆነው ተጫራች ጋር ውል በመያዝ የሚፈፀም የግዥ ስልት ነው።

4/ Joint procurement is a procurement method in which two or more offices, not included in the list issued by the Bureau pursuant to Article 51, Sub-Article (3) of this Proclamation, conclude a contract with the winning bidder based on a bid to meet their common needs.

፭/ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለመንግሥት የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት ባላቸው የስራ ባህርይ ምክንያት በሊዝ ስምምነት መሠረት ግዥ የሚፈፅሙበት ሁኔታ እና ዝርዝር አሠራር በዚህ አዋጅ መሠረት ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

5/ Without prejudice to the provisions of this department, the conditions and detailed procedures for procurement under lease agreements by public bodies due to their nature of work, taking into account the economic benefits to the government, shall be determined by the directives to be issued by the Bureau pursuant to this Proclamation.

፮/ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የራሱን የሰው ኃይልና መሣሪያ በመጠቀም ያለ ጨረታ ሂደት በራሱ ግንባታን ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎት ሥራን የሚያከናውንበት የግዥ ስልት ዝርዝር አፈፃፀም በመመሪያ ይወሰናል።

6/ The detailed implementation of the procurement method, whereby public body uses its own manpower and equipment to carry out construction or non-consultant service work without a bidding process, shall be determined by a directive.

፯/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ራሳቸውን ችለው በተለያየ ጨረታ ሊፈፀሙ የሚችሉ የአንድ ፕሮጀክት አካል የሆኑ ግዥዎችን በማቀናጀት በአንድ ጨረታ መፈፀሙ አዋጭና ጠቀሜታ እንደሚኖረው ሲያምኑ ግዥውን በተርንኪ ግዥ መፈፀም ይችላሉ፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል

7/ Public bodies may, when they believe that it is feasible and beneficial to combine procurements that are part of a project that could be made through separate bid, conduct the procurement through a single bid; the details of which are determined by directives.

፰/ የኤሌክትሮኒክ ልውውጥ ሐራጅ ጨረታ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመጠቀም ተጫራቾች በመሥሪያ ቤቶች ለሚፈለጉ ዕቃዎችና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ዋጋቸውን እየቀነሱ የሚወዳደሩበት ስልት ሲሆን ዝርዝር አሠራሩ በመመሪያ ይወሰናል።

8/ Electronic reverse auction is a method of bidding by electronic means in which bidders compete by reducing their prices for goods and non-consultant services required by offices. The detailed procedure is determined by directives.

ክፍል ስድስት

የመንግሥት ንብረት አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ

፳፱. አጠቃላይ

የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግሥት ንብረት በአግባቡ የመያዝ እና የመጠቀም፣የመከታተል እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በወቅቱ የማስወገድ ተግባር መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፴. ንብረትን የመያዝ ዓላማ

ማንኛውም የመንግሥት ንብረት በባለቤትነት የመያዝ ብቸኛ ዓላማ የፀደቁትን የመሥሪያ ቤቱን ግቦች ለማስፈጸም እና አገልግሎቱን በማፋጠን ውጤታማና ብቁ ለማድረግ መሆን አለበት፡፡

፴፩. አጠቃቀም እና ጥገና

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ፡-

ሀ) በመሥሪያ ቤቱ ሥር ላሉ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች ማሽነሪዎች አገልግሎት የሚውሉ ነዳጅ፣ ዘይትና ቅባቶች፣እንዲሁም ሌላ ማንኛውንም የመንግሥት ንብረት የመሥሪያ ቤቱን ኃላፊነት ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ አገልግሎት ላይ ማዋሉን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ለ) ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ለተሽከርካሪዎች፣ ለማሽነሪዎች እና ሌሎች ቋሚ ንብረቶች ተገቢ የጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

PART SIX

Handling, Use and Disposal of Public Property

29. General

The head of public bodies shall ensure that

Public property is properly held, used, monitored,

and disposed of in a timely manner when necessary.

30. Purpose of Acquisition of Property

The sole purpose of any public property acquisition shall be to achieve the approved goals of the office and to expedite its services, making them more efficient and effective.

31. Use and Maintenance

1/ The head of public body shall:-

A) Ensure that fuel, oil and lubricants used for the service of vehicles and other machinery under the office, as well as any other public property, are used in a manner that effectively carries out the responsibilities of the office.

B) The details of which shall be determined by directives, shall be such that a proper system of maintenance and care shall be established for vehicles, machinery and other fixed assets so that the public property may be used economically and effectively.

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች፣ፕላንቶች እና በከፍተኛ ወጪ የሚገዙ ንብረቶች የመድህን ዋስትና ሽፋን እንዲያገኙ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

፫/ ከቢሮዉ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር የተሽከርካሪ፣ የማሽነሪ፣ እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ ንብረቶችን አካል ፈታትቶ ለሌላ ቋሚ ንብረት አካል አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

፴፪. የመንግሥት ንብረት ስለማስተዳደር

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ:-

ሀ) የመንግሥት ንብረት አስተዳደር የሕይወት ዘመን ሥርዓትን የተከተለ መሆኑን፣

ለ) በመሥሪያ ቤቱ ሥር ያለ የመንግሥት ንብረት ከተያዘበት፣ ከአገልግሎት ውጪ እስከሆነበት ቀን ድረስ ንብረቱ አገልግሎት ያቋረጠበትን ጊዜ፣ የንብረቱን ዓይነት፣ ብዛቱን እና ያስከተለውን ወጪ የሚያሳይ ዝርዝር ተመዝግቦ መያዙን፤

ሐ) ማናቸውንም ቋሚ ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት በመጀመሪያ ደረጃ ንብረቱን እንዲገለገለበት ኃላፊነት ለተሰጣቸው ሠራተኞች መሰጠቱን እና በቋሚ ንብረት መዝገብ የጠባቂዎቹ ዝርዝር እና በእነርሱ ጥበቃ ሥር ያሉት ቋሚ ንብረቶች የሚገኙበት ቦታ መመዝገቡን፣

መ) ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የማይውሉ አላቂ ንብረቶች በመሥሪያ ቤቱ የሚመለከተው የንብረት ሥራ ክፍል በንብረት ዝርዝር መዝገብ ውስጥ መካተታቸውንና ለጥበቃቸው ኃላፊ መመደቡን፣

2/ public properties may provide insurance coverage for vehicles, machinery, plants and other fixed assets purchased at high cost.

3/ It is prohibited to disassemble and use parts of vehicles, machinery, and electronic assets as part of other fixed assets unless permission is granted by the bureau.

32. Administration of Public Property

1/ The head of a public body:-

A) Whether the administration of public property follows the life cycle system;

B) A record is kept of the date on which the asset under the administration of the government is taken into custody, the date on which the property is taken out of service, the type of asset, the quantity and the cost incurred;

C) The responsibility for the maintenance of any fixed asset is assigned to the employees who are primarily responsible for the maintenance of the asset and the list of the custodians and the location of the fixed asset under their care is recorded in the fixed asset register;

D) Ensure that non-current assets that are not immediately available are included in the property inventory of the relevant property administration department of the office and that a person is assigned to their care;

.

ሠ) ልዩ ቋሚ ንብረቶች በተጠቃሚዎች ካርድ ላይ ተመዝግበው የተለየ ቁጥጥር የሚደረግባቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

E) Ensure that special fixed assets are recorded on the user card and are subject to special control.

፪/ ማንኛውም የመንግሥት ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መቆጠር አለበት፡፡

2/ Any public property shall be valued at least once a year.

፫/ የመንግሥትን ንብረት ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን ሳይቻል ሲቀር ግምቱ በዚህ አዋጅ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

3/ If it is not possible to determine the actual value of public property, the valuation shall be determined in accordance with the directives issued by this proclamation.

፬/ በመንግሥት ቋሚ ንብረት ላይ የእርጅና ቅናሽ ይሰላል፡፡

4/ Depreciation value shall be calculated on public fixed assets.

፭/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተፈጥሯዊ ባህርያቸው ምክንያት በትነት እና በፍሳሽ የሚፈጠሩ ብክነቶችን ለማካካስ ለዚህ ዓላማ ማስፈፀሚያ በዚህ አዋጅ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

5/ Public bodies shall implement the implementation of this purpose in accordance with the directives issued in this proclamation to compensate for losses caused by evaporation and leakage due to their natural characteristics.

፴፫. መጠበቅና መንከባከብ

ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ተረክቦ የሚገለገልባቸውን የመንግሥት ንብረቶች የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት፡፡

33. Protection and Preservation

Every government employee is responsible for the safekeeping and maintenance of public property entrusted to him.

፴፬. የመንግሥትን ንብረት ስለማስወገድ

የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ለመሥሪያ ቤቱ አገልግሎት የማይሰጡ የመንግሥት ንብረቶችን በዚህ አዋጅ መሠረት በወቅቱ መወገዳቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

34. Disposal of Public Property

The head of public body shall ensure that public property that is no longer used for the office's purposes is disposed of in a timely manner in accordance with this Proclamation.

፴፭.ንብረትን ስለማስወገድ መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች

ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ንብረት ማስወገድ የሚችለው ከሚከተሉት ዉስጥ አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ተሟልተዉ ሲገኝ ብቻ ነው፡-

፩/ ንብረቱ ለመሥሪያ ቤቱ ዓላማዎች የማይፈለግ ሲሆን፤

፪/ ንብረቱን ይዞ መቀጠል የሚያስከትለው ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ ንብረቱን ማስወገድ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ሲገኝ፤

፫/ በልዩ ልዩ ምክንያት ንብረቱ የሚፈለግበትን አገልግሎት በብቃት መስጠት የማይችል ወይም ከአገልግሎት ውጪ ሲሆን፤ ወይም

፬/ መሥሪያ ቤቱ ከሚኖረው የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ዕቅድ ንብረት ትርፍ መሆኑ ሲታመን፡፡

35. Conditions to be met for disposal of property

Any public body may dispose of property only if one or more of the following conditions are met:

1/ The property is no longer required for the purposes of the office;

2/ The cost of maintaining the asset is so high that it is preferable to dispose of the property;

3/ For various reasons, the property is no longer capable of providing the service required or is no longer in service; or

4/ When it is believed that the profit is from the property of the office's short, medium and long-term business plan.

፴፮. የተፈቀዱ የንብረት ማስወገጃ ዘዴዎች

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ንብረት በሚያስወግዱበት ወቅት የሚከተሉትን አሠራሮች መከተል ይኖርባቸዋል፡-

፩/ በማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ይዞታ ሥር ያለን ንብረት ለማስወገድ እንደ ንብረቱ ባህርይ የሚከተሉት የንብረት ማስወገጃ ዘዴዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፡-

ሀ) ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በማዛወር ወይም በማስተላለፍ፤

36. Authorized Methods of Property Disposal

Public bodies should follow the following procedures when disposing of property:

1/ The following methods of disposal shall be used to dispose of property held by any Public body, depending on the nature of the property:

A) By transferring or adjournal conveying it to another Public body,

ለ)ባለቤት ሁኔታ ወይም እንደ ሁኔታው ፈታሹ ለሕዝብ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት በጨረታ ወይም በሐራጅ በመሸጥ፣

ሐ) ንብረቱን በስጦታ በማስተላለፍ፣

መ) ንብረቱን በመቅበር ወይም በማቃጠል፣

ሠ) ንብረቱን በማፈን፣ በማምከን ወይም በመቀየጥ፣ ማስወገድ፡፡

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከላይ በተቀመጡ ማስወገጃ ዘዴዎች ንብረት ሲያስወግዱ ለመልሶ መጠቀም ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፡፡

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተቀመጡት የንብረት ማስወገጃ ዘዴዎች የተወገዱ ንብረቶችን ዝርዝር፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ከማስወገድ የተገኘውን ገቢ የሚያሳይ ሪፖርት ለቢሮዉ መላክ ይኖርባቸዋል፡፡

፴፯. ንብረትን በማስወገድ ሂደት ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

ዝርዝር አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ንብረትን በማስወገድ ሂደት የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ አለበት፡-

፩/ የንብረቱ ሕጋዊ ባለቤት ማን እንደሆነ መለየት፤ በይዞታው ሥር ለሚገኝ ንብረት የባለቤትነት ማስረጃ ማቅረብ የማይችል ከሆነ በገዥው ላይ ለሚቀርብ የይገባኛል ጥያቄ ዋቢ በመሆን ንብረቱን ማስወገድ፤

፪/ ሕንፃና ተመሳሳይ ግንባታዎች የባለቤትነት መብት የተሰጠው ለክልሉ መንግሥት በመሆኑ እነዚህን ንብረቶች ማስወገድ የሚፈልግ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቢሮዉን ማስፈቀድ፤

B) By selling it, to the public through an electronic auction or bid system,

C) By transferring the property as a donation,

D) Dispose of the property by burying or burning it;

E) Dispose of the property by smothering, sterilizing or converting it.

2/ Public bodies must give priority to recycling when disposing of property by the above-mentioned disposal methods.

3/ Public bodies shall send to the Bureau a list of property disposed of through the property disposal methods set forth in Sub-Article (1) of this Article, as well as a report showing the proceeds from disposal in accordance with Sub-Article (2) of Article 39 of this Proclamation.

37. Precautions to be taken during the process of property disposal

The details of which shall be determined by the property administration directives issued pursuant to this proclamation, any government office shall take the following precautions during the process of disposing of property:

1/ Identify the legal owner of the property; if he is unable to provide proof of ownership of the property under his possession, dispose of the property as a reference for a claim against the purchaser;

2/ Since the ownership of buildings and similar structures is vested in the regional government, any government office wishing to dispose of these property shall authorize the bureau;

፫/ የሚወገዱት ንብረቶች በባህርያቸው ልዩ ጠቀሜታ ያላቸው ወይም በጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች፣ የኬሚካል ውጤቶች እና ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ የኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች፣ መድኃኒቶች፣ ጨረር አመንጪ ወይም የመሳሰሉት ሲሆኑ በአወጋገዱ ላይ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር ወይም አስፈላጊውን እገዛ በመጠየቅ ማስወገድ፡፡

3/ The properties to be disposed of are expired chemicals, chemical products, and obsolete electronic devices, medicines, radiation emitters, or the like, which are of special importance or harmful to health or the environment, and should be disposed of in consultation with the relevant body or by requesting the necessary assistance.

፴፰. ንብረትን በማስወገድ ስለሚገኘው ገቢ

38. The income from the disposal of property

፩/ በፋይናንስ አስተዳደር ሕጉ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ንብረት በማስወገድ የተገኘው ገቢ ንብረቱን የሚያስወግደው የባለበጀት መንግሥት መሥሪያ ቤት ሲሆን ለመንግስት ትሬዥሪ ገቢ ሆኖ አፈፃጸሙ በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሲሆን ለድርጅቱ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

1/ Without prejudice to the provisions of the Financial Administration Law, the income from the disposal of public property shall be transferred to the budget office of the government and shall be allocated to the government treasury as revenue, as determined by directives, and shall be transferred to the organization in the case of a government development organization.

፪/ ንብረቱን የሚያስወግደው በመንግሥት በጀት የሚተዳደር የመንግስት መሥሪያ ቤት ሲሆን የተወገደው የመንግሥት ንብረት መግለጫ እና ንብረቱን በማስወገድ የተገኘው ገንዘብ በዓመታዊ የመንግሥት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ መጠቃለል አለበት፡፡

2/ The property shall be disposed of by a public body managed by the public budget, and a description of the public property disposed of and the income from the disposal of the property shall be included in the annual government accounting report.

፴፱. መሠረዝ

39. Write off

፩/ ማንኛውም የመንግሥት ንብረት፡-

1/ Any public property:-

ሀ) ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የማይጠቅምና ዋጋ የማያወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

A) When it is proven that it is of no use or value to the public body or any other government office;

ለ) ከጥቅም ውጪ ሲሆን ወይም ሲጎድል፣

B) When it is out of use or missing,

ሐ) ሲሠረቅ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ምክንያት ሲጠፋ ወይም ሲቃጠል እና በሚመለከተው የሕግ አካል ሲረጋገጥ፣ ከንብረት መዝገብ ይሠረዛል፡፡

C) When it is stolen or destroyed for any other similar reason or burned and is verified by the relevant legal body, it shall be deleted from the property register.

፪/ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ሲሰረዝ መግለጫውና የንብረቱ መዝገብ ዋጋ ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በዓመታዊ የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ተጠቃልሎ መታየት አለበት፡፡

2/ When any public property is liquidated, the description and the value of the property must be included in the annual government accounts report in accordance with the directive issued by the bureau.

፵. ማስተላለፍ እና ስጦታ

40. Transfer and Donation

ቢሮዉ ለክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ለዞኖች ለወረዳዎች፣ ለከተማ አስተዳደሮች እና ለማዘጋጃ ቤቶች በማስተላለፍ፣ እንዲሁም ለሌሎች የመንግሥትን ኃላፊነት የማገዝ ተግባር ለሚያከናውኑ አካላት በስጦታ የሚተላለፉበትን ሁኔታ በመመሪያ ይወስናል፡፡

The Bureau shall determine by directive the conditions for the transfer of properties not used by regional public bodies to zones, weredas, city administrations, and municipalities, as well as the conditions for the transfer of properties as donations to other entities performing government duties.

ክፍል ሰባት

የጨረታ ሥነ-ሥርዓት

PART SEVEN

Bid Procedure

፵፩. የጨረታ ማስታወቂያ

41. Advertisement of Bid

፩/ የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀበት ቋንቋ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ወይም እንደአግባብነቱ በሌሎች ዘዴዎች በመጠቀም ይፋ መሆን ይኖርበታል፡፡

1/ The advertisement of bid shall be notified in the language in which the bid document was prepared, electronically or by other means as appropriate.

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈፃፀም ጨረታው አየር ላይ የሚውልበት ጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የጨረታ ማሻሻያ ሊኖር እንደሚችልና ተጫራቾችም ይህን ክትትል እንዲያደረጉ የሚገልፅ ማስታወቂያ ይፋ በሚሆንበት ዘዴ መገለፅ ይኖርበታል፡፡

2/ The implementation of Sub-Article 1 of this Article shall include a method of publication of an advertisement stating that the bid may be modified until the end of the bid opening period and that bidders shall be informed of this.

፫/ ለተወዳዳሪዎች ለመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የሚሰጠው ጊዜ በግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር መመሪያዎች ከሚወሰነው አነስተኛ የቀን ብዛት ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

፬/ የጨረታ ማስታወቂያ በአየር ላይ የሚቆይበት የጊዜ ሰሌዳ እንደሚመረጠዉ የግዥ ዘዴ አይነት ቢሮዉ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

3/ The time allowed for candidates to submit their bid proposals shall not be less than the minimum number of days specified in the Procurement and Property Administration Directives.

4/ The schedule for the publication of the bid notice shall be determined by the directives issued by the Bureau, depending on the type of procurement method chosen.

፵፪. የጨረታ ሰነድ

42. Bid Document

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተጫራቾች መካከል የሚደረገው ውድድር በተሟላና ወጥነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ የሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ በቢሮዉ የተዘጋጀውን ወይም የፀደቀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1/ In order to ensure that the competition among bidders is conducted in a complete and consistent manner, the bid document prepared by public bodies must be based on the standard biddocuments prepared or approved by the bureau.

፪/ የጨረታ ሰነዱ የጨረታው ማስታወቂያ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ጨረታው እስከሚዘጋበት ጊዜ ድረስ ባሉት ቀናት እና በጨረታ ማስታወቂያው በተገለፀው አኳኋን ለተወዳዳሪዎች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ተደራሽ መደረግ አለበት፡፡

2/ The bid document shall be made available to the candidates electronically from the date of publication of the bid notice until the date of closing of the bid and in the manner specified in the bid notice.

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት እና ሰነዱን ለተወዳዳሪዎች ለማቅረብ የሚያወጡትን ወጪ ለመተካት ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

3/ Public bodies may charge a fee to cover the costs incurred in preparing the bid document and providing it to the candidates.

፵፫. በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታና ስለሚደረግ ማሻሻያ

43. Regarding complains and modification to the bid document

፩/ ማንኛውም ተወዳዳሪ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚያወጧቸው የጨረታ ማስታወቂያዎች እንዲሁም የጨረታ ሰነዶች ይዘት ላይ ማብራሪያ ሊጠይቅ ወይም ቅሬታ ኑሮት ምላሽ ካልተሰጠው ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

1/ Any candidates may request clarification on the content of the bid notices as well as bid documents issued by public bodies or may file an appeal if the complaint is not responded to.

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በራሳቸው ወይም ከተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻ የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ በፊት የጨረታ ሰነዶችን ይዘት ለማሻሻል ይችላሉ፡፡

፫/ የተደረገው ማሻሻያ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መውጣት ያለበት ሲሆን በተጨማሪም በጨረታ ሰነዱ ላይ ማሻሻያ ስለመደረጉ መገለፅ አለበት፡፡

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የጨረታ ሰነዱን ይዘት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እና በማሻሻያው የተመለከቱ ማስተካከያዎችን ለማድረግ በቂ ጊዜ የሌለ መሆኑን ሲረዳ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነዳቸውን አሻሽለው ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግ የጨረታ ማቅረቢያ ጊዜውን ቢያንስ ለ፭ (አምስት) ተጨማሪ የሥራ ቀናት ማራዘም አለበት፡፡

፭/ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተደረገ ማሻሻያ ወይም ለቀረቡ የማብራሪያ ጥያቄዎች በተሰጠ ምላሽ ላይ ተወዳዳሪዎች ቅሬታ ያላቸው እንደሆነ ለይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ አካል ይግባኛቸውን ለማቅረብ እንዲያስችላቸው መሥሪያ ቤቱ ምላሽ ከሰጠበት ወይም ምላሽ ሊሰጥ ይገባው ከነበረበት ቀን አንስቶ ለ 5 የሥራ ቀናት ጨረታው ሳይዘጋ ማቆየት ወይም የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም አለበት፡፡

፵፬. የጨረታ ማስከበሪያ

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ላይ ተጫራቾች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር የጨረታ ማስከበሪያ ወይም እንደሁኔታው የጨረታ መተማመኛ ቅጽ ሞልተው የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡

2/ Public bodies may modify the content of the bid documents before the deadline for submission of bidding proposals, either on their own initiative or based on requests from candidates.

3/ The modification made must be submitted electronically and also be stated in the bid document.

4/ When the public bodies finds it necessary to modify the content of the bidding document and realizes that there is insufficient time to make the necessary adjustments, it shall extend the bid submission period for at least 5 (five) additional working days to allow candidates sufficient time to modify their bidding proposals.

5/ The detailed implementation shall be determined by the directive. If the bidders have any complaints regarding the amendment made to the bidding document or the response given to the clarification questions submitted, the public bodies shall keep the bid open or extend the bid closing date for 5 working days from the date on which the office responded or should have responded, to allow them to file their appeal with the appeals and decision-making body.

44. Bid Security

1/ Public bodies shall state in the bidding documents prepared by them that bidders are required to submit a completed bid security or bid declaration’s form, as the case may be, along with their bidding proposals.

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዋስትናው እውነተኛ መሆኑን ዋስትና ሰጪውን አካል አስቀድመው በመጠየቅ ማረጋገጥ አለባቸው።

2/ Public bodies must verify the authenticity of the guarantee by first asking the guarantor.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ የሚያስፈልገው የዋስትና መጠን እና ዓይነት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል።

3/ The amount and type of security required for a bid security submitted pursuant to sub-article (1) of this Article shall be determined by the directives issued pursuant to this Proclamation.

፬/ በማንኛውም ተጫራች የቀረበ የጨረታ ማስከበሪያ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊወረስ ይችላል፡-

4/ The bid security submitted by any bidder may be forfeited for any of the following reasons:

ሀ. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ጨረታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድድሩ ካገለለ ወይም፣

A. If the bidder withdraws from the competition during the bid validity period after the bid has been opened, or,

ለ. ጨረታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ አሸናፊ ተጫራች መሆኑ በፅሑፍ ተገልጾለት ውል ለመዉሰድ፣ የገዛውን ንብረት ለማንሳት ወይም የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ካልሆነ፣

B. If, during the validity period of the bid, the successful bidder refuses to accept the contract, remove the purchased property, or enter into a contract agreement, in writing,

ሐ. በዚህ አዋጅና በመመሪያው ላይ በሚደነገገው መሠረት ተጫራቹ የሂሳብ እርማት ተደርጎ ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ፤

C. Where the bidder refuses to accept arithmetic correction made in accordance with this Proclamation and the Directive issued hereunder,

መ/ ተጫራቹ የማጭበርበር ወይም የማታለል ወይም ከሌሎች ተጫራቾች ጋር የመመሳጠር ወይም መረጃ የመደበቅ ድርጊቶችን መፈፀሙ ሥልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ ከሆነ።

D) Where the bidder commits fraudulent or deceitful act, collides with other bidders or conceals information and where such act or omission is proved by a competent Authority.

፵፭. የመጫረቻ ሰነድ ስለማቅረብና ስለመቀበል

45. Submission and Receipt of Bid Proposal

፩/ የመጫረቻ ሰነድ በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት ጨረታ ማስታወቂያው ወይም በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች በተገለፀዉ መሰረት እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት መቅረብ አለበት።

1/ Bidding proposal must be submitted electronically as specified in the bidding notice or other means of communication and before the deadline specified in the bid documents.

፪/ የመጫረቻ ሰነድን ለማቅረቢያ ከተወሰነው ጊዜ በኋላ የሚቀርብ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

፫/ ተጫራቾች በጨረታ ማስታወቂያ ላይ በተገለፀው የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ የማሻሻያ ሰነድ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

፵፮. ጨረታን ስለመክፈት

፩/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታ ሰነዱ የተመለከተው የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የመጫረቻ ሰነድን በጨረታ መክፈቻ ቀንና ስዓት ጠብቆ መክፈት አለበት፡፡

፪/ የተጫራቹ ስም እና በእያንዳንዱ የመጫረቻ ሰነድ የቀረበው የመጫረቻ ዋጋ፣ የተሰጠ ቅናሽ እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እንደ ግኝው ሁኔታ ተጫራቾች አንፃራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ብሎ የሚያምንባቸውን ሌሎች መረጃዎች እንዲመዘገብ እና ተጫራቾች የተመዘገበውን ዝርዝር እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የቴክኒክና የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ተለይቶ የቀረበ በሚሆንበት ጊዜ ተጫራቾች ያቀረቡት ዋጋ የሚከፈተው የቴክኒክ ግምገማው ከተጠናቀቀና ወደሚቀጥለው የውድድር ክፍል የተሸጋገሩት ተጫራቾች ከታወቁ በኋላ ይሆናል፡፡

፵፯. የመጫረቻ ሰነዶችን ስለመመርመር እና ስለመገምገም

፩/ ጨረታውን ለመመርመርና ግምገማውን ለማከናወን የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ተጫራቾች ባቀረቡት የመጫረቻ ሰነድ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2/ Any document submitted after the deadline for submission of a bidding proposal will not be accepted.

3/ Bidders may submit modified bidding proposal within the bid submission period specified in the bid notice.

46. Opening of Bids

1/ After the closing date for submission of bid proposals, the public body shall open all bid proposals received before the closing date, at the time and date stated in the bid document and in the invitation to bid for opening of bids.

2/ The name of the bidder and the bid price offered in each bidding proposals, any discounts offered and other information that the public body believes will help bidders determine their relative position in the procurement, shall be recorded and bidders shall have access to the recorded list.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this article, where the technical and financial bids thought are submitted separately, the prices offered by the bidders shall be opened after the technical evaluation is completed and the bidders who have advanced to the next stage of the competition are identified.

47. Examination and evaluation of bid proposals

1/ When it is deemed necessary to examine and evaluate the bid, the public body may request bidders to provide clarifications on the bidding proposals submitted.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም የዋጋ ለውጥን ጨምሮ የመጫረቻ ሰነዱ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ሀሳብ ማቅረብ ወይም መፍቀድ አይቻልም፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this article, no proposal shall be made or permitted to make any fundamental changes to the bidding proposal, including price changes.

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታ ግምገማ ወቅት የተገኙ የሂሳብ ስህተቶችን ማረምና የተደረገውን ማስተካከያ ለሚመለከተው ተጫራች በአፋጣኝ መግለፅ አለበት፡፡

3/ The public body shall promptly correct arthimatic errors found during the evaluation of the bids and shall promptly notify the bidder concerned of the corrections made.

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የመጫረቻ ሰነዱ የተሟላ ነው ብሎ ሊቀጥል የሚችለው በጨረታ ሰነዱ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ነው፡፡

4/ The public body may consider the bidding proposals to be complete only if it finds that they meet the requirements set out in the bidding documents.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጨረታው ሰነድ ከተዘረዘሩት ባህሪያት፣ የውል ቃሎች፣ ሁኔታዎች እና ሌሎችም ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረውም፣ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡

5/ Without prejudice to the provisions of sub-article (4) of this article, the public body may accept the bid as complete even if it differs to some extent from the characteristics, terms, conditions and other required points specified in the bidding document, provided that there is no fundamental change or difference, or even if there is a minor error or omission that can be corrected without changing the substance of the bid.

፮/ ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች በአንዱ ተጫራችን የጨረታው አሸናፊ አድርጎ መምረጥ የለበትም፡-

6/ The Public Body shall not pronounce a bidder to be the successful bidder on any of the following grounds:

ሀ) ተጫራቹ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፮. ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

A) When the bidder is found unable to meet the requirements specified in Article 16. Sub-Article (1) of this Proclamation;

ለ) ተጫራቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተደረገውን የሂሳብ ማስተካከያ የማይቀበል ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም የሂሳብ ስህተቱ በመመሪያው ወይም በጨረታ ሰነዱ ላይ ከሚቀመጠው ገደብ ውጭ ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ) የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ ሰነዱ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ፣

መ) አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጡ መመዘኛዎች መሠረት በሚደረግ ግምገማ ተጫራቹ የሚገባውን ውል ለመፈፀም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ መሣሪያ፣ በቂ የአገልግሎት መስጫ ስፍራ፣ ግዥው በሚፈፀምበት ዘርፍ የሥራ አመራር ችሎታ እና ልምድ፣ መልካም ሥራ አፈፃፀም እና ብቃት ያለው የሰው ኃይል የሌለው ሆኖ ሲገኝ፣

ሠ) የተለየ አስተያየት ለማግኘት ወይም ጨረታውን ለማሸነፍ ለማናቸውም ኃላፊ ወይም ሠራተኛ መደለያ መስጠቱ ወይም የመደለያ ሀሳብ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣

ረ) የግዥ ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፷፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ቢሮው በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ጨረታ እንዳይሳተፍ ዕገዳ የተጣለበት ድርጅት፣

B) When the bidder does not accept correction of arithmetical error made in accordance with sub-article (3) of this article, or when the calculation error is found to be outside the limits set out in the directives or the bidding document;

C) When the submitted bidding proposals does not meet the conditions specified in the bidding document;

D) When, based on the criteria set out in the bid document, the bidder is found to lack the professional and technical qualifications, financial capacity, equipment, adequate service facilities, management skills and experience in the sector in which the procurement is to be carried out, good work performance, and competent manpower to perform the contract,

E) When it is proven that any official or employee has been bribed or offered bribery to obtain a different opinion or to win the bid,

F) An organization that has been banned from participating in any public procurement tender pursuant to a decision issued by the Bureau pursuant to Article 63, Sub-Article (2), Letter (a) of this Proclamation after the commencement of the procurement process;

ሰ) ተወዳዳሪው በጨረታው ሰነድ ላይ የማጭበርበር ተግባር መፈፀሙ፣ ወይም ከሌላ ተወዳዳሪ ጋር መመሳጠሩ ሲረጋገጥ ወይም በጨረታ ሰነዱ ወይም መመሪያው ላይ በሚገለፀው መሠረት የጥቅም ግጭት ያለበት ሆኖ ከተገኘ ወይም ሌሎች ከሥነ-ምግባር ውጪ የሆኑ ድርጊቶች ፈፅሞ ሲገኝ፣

G) If the candidates is found to have committed fraud in the bidding document, or colluded with another candidates, or is found to have a conflict of interest as described in the bidding document or directives, or if any other unethical conduct is found to have been committed;

፯/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) በተደነገገው መሠረት አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው የግምገማ መስፈርት መሠረት ተፈላጊውን ያሟሉ የመጫረቻ ሰነዶችን መገምገምና ማወዳደር አለበት፡፡ በጨረታ ሰነድ ያልተመለከተ የማወዳደሪያ መስፈርት በጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡

7/ The public body shall evaluate and compare the bid documents that meet the requirements in accordance with the evaluation criteria specified in the bidding proposals to select the winning bidder, as provided for in sub-article (9) of this article. Comparison criteria not specified in the bidding document may not be used.

፰/ በዚህ አዋጅ በግልፅ ካልተመለከተ በስተቀር ማናቸውም ተጫራች በመጫረቻ ሰነዱ ከተመለከተው ውጪ በጨረታው አሸናፊ ለመሆን ያቀረበውን የመጫረቻ ዋጋ እንዲለውጥ ወይም ያቀረበውን የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያሻሽል ወይም ይህንን ለመፈፀም ግዴታ እንዲገባ ሊጠየቅ ወይም ሊገደድ አይችልም፡፡

8/ Unless otherwise expressly provided in this Proclamation, no bidder shall be required or compelled to change the bid price or modify the proposal submitted by him in order to win the bid, or to undertake any obligation to do so, other than as specified in the bidding proposal.

፱/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጨረታ ውድድሩ ከቀረቡ ተጫራች መካከል አሸናፊ የሚሆነውን ተጫራች ለመለየት፡-

9/ In order to identify the winning bidder among the bidders submitted in the bidding competition, public bodies shall:

ሀ) በጨረታ ሰነድ ላይ የተመለከቱትን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርቶች ማሟላቱ በቅድሚያ ከተረጋገጠ በኋላ እንደ ግዥው ባህሪ አነስተኛ ዋጋ ያቀረበን ተጫራች፣ ወይም በነጥብ አሰጣጥ የግምገማ ዘዴ በቴክኒክና በዋጋ ጠቅላላ ድምር ውጤት ከፍተኛውን ነጥብ ያገኘን ተጫራች አሸናፊ አድርገው ሊመርጡ ይችላሉ፣

ለ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንደ ግዥው ባህሪ እና ዓይነት የሕይወት ዘመን ወጪ ትንትና ሥርዓትን መጠቀም አለባቸው፡፡

፲/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት በአሸናፊነት የተመረጠ ተጫራች በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ተገምግሞ ያለፈ ካልሆነ በስተቀር እንደአስፈላጊነቱ ሕጋዊነቱ እንዲሁም የፋይናንስ እና የቴክኒክ አቅሙ በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት መሆኑ በድህረ-ግምገማ መረጋገጥ አለበት፡፡

፲፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የግምገማውን ሂደትና ውጤት የሚገልፅ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡

A) After first verifying that the minimum technical requirements specified in the bidding document are met, the bidder who submitted the lowest price, depending on the nature of the procurement, or the bidder who obtained the highest score in the total score of technical and price in the scoring evaluation method, may be selected as the winner;

B) Without prejudice to the provisions of letter (a) of this sub-article, government offices shall use a life-cycle cost analysis system, depending on the nature and type of procurement.

10/ Unless a successful bidder has been evaluated in a pre-qualification bid in accordance with sub-article (9) of this article, its legality and financial and technical capacity shall be verified, as necessary, through a post-evaluation, in accordance with the evidence provided in the bidding proposals.

11/ The public body shall prepare an evaluation report describing the process and results of the evaluation.

፵፰. የጨረታን ሂደት በሚስጥር ስለመጠበቅ

ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ከጨረታ ምርመራ፣ ከማብራሪያ ከግምገማ እና አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር የተያያዙ መረጃዎች በሚስጥርነት መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን አሸናፊው ተጫራች እስከሚገለፅ ድረስ ለተጫራቾች ወይም ከሥራው ሂደት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች መግለፅ የለባቸውም፡፡

48. Confidentiality of Bid Proceeding

From the time the bid is opened, information related to the bid examination, explanation, evaluation, and the decision regarding the winning bidder must be kept confidential and must not be disclosed to bidders or persons not involved in the bidding process until the Winning bidder is announced.

፵፱. ከአሸናፊ ተጫራች ጋር ድርድር ስለሚደረግባቸው ጉዳዮች

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር መሠረታዊ ባልሆኑ የውል አፈፃፀም ጉዳዮች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከተው ቢኖርም በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአሸናፊው ተጫራች መካከል በሚደረገው ድርድር መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚስማማባቸው የውል ቃላት እና ቅድመ ሁኔታዎች ለተጫራቹ የተለየ ጥቅም የማይሰጡ እና መሥሪያ ቤቱንም የማይጎዱ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፮ ላይ በተጠቀሰው መሠረት ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ለሚፈፀም ግዥ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ በተለይ ካልተፈቀደ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አሸናፊ ተጫራቾች ባቀረቡት ዋጋ እና ዋጋን በተመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ድርድር ማድረግ አይችልም፡፡

፶. የጨረታ ውጤትና አሸናፊነትን ስለመግለፅ

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከተጫራቾች የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የጨረታውን ዝርዝር ውጤት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ወይም ስርዓቱ ያልተዘረጋባቸዉ ከሆነ በማስታወቂያ እና በደብዳቤ ወይም ሌሎች መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም በጨረታው ለተሳተፉ በሙሉና ለሕዝብ በተመሳሳይ ጊዜ ይፋ ማድረግ አለባቸው፡፡

፪/ ተጫራቾች በጨረታው ውጤት የማይስማሙ ከሆነ በዚህ አዋጅ ላይ የተገለፀውን የአቀራረብ ሥርዓት በተከተለ መንገድ አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን የሚገልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡

49. Matters subject to negotiation with the Successful Bidder

1/ The public body may negotiate with the winning bidder on non-fundamental matters of contract performance.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this article, the terms and pre-conditions agreed upon by the public body in the course of negotiations between the public body and the successful bidder shall ensure that they do not give any special advantage to the bidder and do not prejudice the office.

3/ Except as specifically permitted by the directives issued pursuant to this Proclamation, for a procurement directly from a single supplier as referred to in Article 26 of this Proclamation, the pubic body shall not negotiate the price offered by the winning bidders and other matters related to the price.

50. Notification of Bid Evaluation Results And Award of Contract

1/ Pubic body must simultaneously announce the detailed results of the bid to all participants in the bid and to the public through an electronic system or, if the system is not implemented, through a notice and letter or other means of communication, before the expiration of the period during which the bid documents submitted by the bidders are valid.

2/ It shall be stated that if the bidders do not agree with the results of the bid, they may submit a complaint in accordance with the procedure set out in this Proclamation.

፫/ በዚህ አዋጅ ለአቤቱታ ማቅረቢያ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካበቃ በኋላ ወይም አቤቱታ ቀርቦ የመጨረሻ እልባት ካገኘ በኋላ ወዲያውኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በአሸናፊነት ለተመረጠው ተጫራች የአሸናፊነት ማስታወቂያ መላክ አለበት፡፡

፬/ የአሸናፊነት ማስታወቂያ ተጫራቹ ያሸነፈበትን ጠቅላላ የዋጋ መጠን፣ ውሉ የሚፈረምበትን ቀን፣ ተጫራቹ ማስያዝ ያለበትን የውል ማስከበሪያ ዓይነት እና መጠን እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በአሸናፊው ተጫራች ሊሟሉ የሚገባቸውን ሌሎች ቅድመ-ሁኔታዎች የሚገልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡

፭/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለተጫራቾች የጨረታውን ውጤት ከማሳወቁ በፊት እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሰረት የሚወሰነው የአቤቱታ ወይም የይግባኝ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ውል መፈረም የለበትም፡፡

ክፍል ስምንት

የማዕቀፍ እና ስትራቴጂያዊ ግዥዎች

፶፩. የማዕቀፍ እና ስትራቴጂያዊ ግዥዎች

፩/ በማዕከል የሚፈፀሙ የማዕቀፍ እና ስትራቴጂያዊ ግዥዎች የሚከናወኑት እንዲሁም በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸው የመንግሥት ንብረቶች በሽያጭ የሚወገዱት በቢሮው ውሳኔ ይሆናል፡፡

3/ The Pubic body shall immediately send a notice of award to the successful bidder after the deadline for filing a set forth in this proclamation has expired or after the complain has been filed and is finally resolved.

4/ The notice of award shall state the total amount of the contract price won by the bidder, the date on which the contract is to be signed, the type and amount of contract security to be provided by the bidder, and any other pre-conditions to be met by the successful bidder, as applicable.

5/ No contract shall be signed before the public body notifies the bidders of the results of the bid and before the deadline for filing a complaint or appeal, as determined in accordance with the regulations issued by the Regional Administrative Council pursuant to this Proclamation.

PART EIGHT

Framework and Strategic Procurement

51. Framework and Strategic Procurement

1/ Framework and strategic procurements carried out at the center, as well as the disposal of Pubic properties decided to be disposed of by Pubic bodies, shall be decided by the bureau.

፪/ ቢሮዉ ግዥው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ፍላጎትና የሥራ ባህሪ ያገናዘበና በሌላ የግዥ አማራጭ ሊፈፀም የማይችል መሆኑን በማረጋገጥ ክልላዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆናቸው ምክንያት የሚፈፀሙ ስትራቴጂያዊ ግዥዎችን ይወስናል፡፡

2/ The Bureau shall determine strategic procurements that are of regional importance, ensuring that the procurement takes into account the needs and working characteristics of public bodies and cannot be carried out through other procurement options.

፫/ ቢሮዉ ግዥ ያቸው በማዕከል የሚፈፀሙ የማዕቀፍ ዕቃዎችንና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶችን፣ እንዲሁም በማዕከል የሚወገዱ ንብረቶችን ዝርዝር በየጊዜው ይወስናል፡፡

3/ The Bureau shall periodically determine the list of framework goods and non-consultative services to be procured centrally, as well as the properties to be disposed of centrally.

፶፪. የማዕቀፍ ስምምነት አፈፃፀም

52. Implementation of Framework Agreement

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚኖራቸው ተመሳሳይ የግዥ ፍላጎት ወይም አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ ለሚኖረው ፍላጎት ግዥውን በማዕቀፍ ስምምነት መፈፀም ይችላል፡፡

1/ For similar procurement needs of public bodies or for a public bodies that has a recurring need over a certain period of time, the procurement may be carried out through a framework agreement.

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሥራቸው ባህሪ ምክንያት የሚጠቀሙባቸው በየጊዜው ከጥቅም ውጭ የሚሆኑ ተመሳሳይ ንብረቶችን ወይም ተረፈ ምርቶችን ሽያጭ በማዕቀፍ ስምምነት ማስወገድ ይችላሉ፡፡

2/ Public bodies may dispose of similar assets or surplus products that are used periodically due to the nature of their work and which are no longer useful, through a framework agreement.

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ቢሮዉ በሚያወጣው ዝርዝር ውስጥ ለተካተቱት ዕቃዎችና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች የሚኖራቸውን የፍላጎት ትንበያ እንዲሁም በማዕቀፍ ሊወገዱ የሚገባቸውን ንብረቶች ዝርዝር አዘጋጅተው በመላክ ለቢሮው ያሳውቃሉ፡፡

3/ Public bodies shall prepare and notify to the bureau a list of the goods and non-consumable services included in the list issued by the bureau, as well as a list of properties to be disposed of under the framework.

፬/ ቢሮው በዚህ አዋጅ በተመለከተው እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ላይ በሚገለፀው ዝርዝር መሠረት በማዕከል የሚፈፀም ግዥ የማዕቀፍ ስምምነት ይፈፅማል፤ ያስተዳድራል።

4/ The Bureau shall implement and manage the procurement framework agreement to be executed centrally in accordance with the details specified in this Proclamation and the directives issued pursuant to this Proclamation.

፭/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የሚፈረመውን የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት በማድረግ ከማዕቀፍ አቅራቢዎች ጋር ዝርዝር ውል ይፈፅማሉ፤ የፈፀሙትን ውልም ያስተዳድራሉ።

5/ Public bodies shall implement and manage the contracts implemeted with the framework providers based on the framework agreement to be signed in accordance with Sub-Article (4) of this Article.

፮/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ በተመለከተው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር በማዕቀፍ ስምምነቱ የአጠላ ዋጋ ወይም መሠረታዊ በሆኑ ሌሎች የስምምነቱ የውል ሁኔታዎች ላይ ለውጥ ማድረግ አይፈቀድም፤ ሆኖም በማዕቀፍ ስምምነቱ ያልተካተቱ እና በማዕቀፍ ስምምነቱ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የማያስከትሉ ጉዳዮች የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በሚገቡት ዝርዝር ውል ሊወሰኑ ይችላሉ።

6/ Except as provided in the directives issued pursuant to this Proclamation, no changes shall be permitted to the unit price or other fundamental terms of the framework agreement; however, matters not included in the framework agreement and not resulting in a fundamental change to the framework agreement may be determined in the detailed contract between the Public body and the framework agreement provider.

፯/ በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ካልተፈቀደ በስተቀር የማዕቀፍ ስምምነት የሚፈፀመው በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ ከተመረጡ ተጫራቾች ጋር ይሆናል።

7/ Unless otherwise permitted by this Proclamation or the Procurement Implementation Directives to be issued pursuant to this Proclamation, the Framework Agreement shall be concluded with the selected bidders through an open bidding procedure.

፰/ የግዥ እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ የማዕቀፍ ስምምነት ዝርዝር አፈፃፀም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል።

8/ The details of the implementation of the Framework Agreement for the procurement and sale of properties to be disposed of shall be determined by the Directives issued pursuant to this Proclamation.

ክፍል ዘጠኝ

የግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ውል

፶፫. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የግዥ ውል ከመፈረማቸው አስቀድመው ለግዥው አገልግሎት የሚውል በቂ በጀት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚፈፀም ማንኛውም የግዥ ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ውል ወይም የውል ማሻሻያ በጽሑፍ መሆን አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት እንደሁኔታው ከአቅራቢው ወይም ከሚወገድ ንብረት ገዥ ጋር ውል ከመዋዋሉ በፊት ወይም ከተዋዋለ በኋላ በውሉ መሠረት መፈፀም እንዲቻል ለውሉ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፶፬. ውል ስለመፈራረም

፩/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የመደበኛ ጨረታ ሰነዶች አንድ ክፍል የሆነውን አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች የውሉ አካል በማድረግ እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ልዩ የውል ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሰነድ ከአቅራቢው ጋር መፈረም አለበት፡፡

፪/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአሸናፊው ተጫራች መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈፀመ አይቆጠርም፡፡

PART NINE

CONTRACT OF PROCUREMENT AND SALE OF DISPOSABLE PROPERTY

53. General Provisions

1/ Public bodies shall ensure that they have sufficient budget available for the procurement before signing a procurement contract.

2/ Unless otherwise provided in this Proclamation and the directives to be issued pursuant to this Proclamation, any contract or amendment to a contract for the purchase or sale of property executed by a Public body shall be in writing.

3/ Any public body shall, before or after concluding a contract with the supplier or purchaser of the property to be disposed of, as the case may be, ensure that the necessary conditions for the performance of the contract are met in order to enable it to be performed in accordance with the contract.

54. Signing a contract

1/ Any public body shall sign a contract document with the supplier, incorporating the general terms and conditions of the contract, which is a part of the standard bidding documents, and the specific terms and conditions agreed upon.

2/ Unless a contract is signed between the public body and the winning bidder, the contract shall not be deemed to have been concluded merely by the announcement of the winner of the bid.

፫/ በመንግሥት መሥሪያ ቤት እና በአቅራቢው መካከል ውል ተመስርቷል የሚባለው ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች የያዘ ውል ሰነድ ሲፈርሙ ሲሆን፣ የአሸናፊነት ማስታወቂያ ለተጫራቹ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፲፭ (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ውሉን መፈረም አለባቸው፡፡

3/ A contract is considered to be concluded between a public body and a supplier when both parties sign a contract document containing the agreed-upon terms and conditions, and both parties must sign the contract within 15 (fifteen) working days from the date of notification of the winning bidder.

፬/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአሸናፊው ተጫራች መከከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች መብትና ግዴታ በግልፅ ማመልከት አለበት፡፡

4/ The contract concluded between the public body and the winning bidder must clearly state the rights and obligations of both parties.

፭/ ቢሮዉ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት መመርመር አያስፈልጋቸዉም ተብለዉ ከሚገለጹ በስተቀር ማናቸዉም የግዥ ዉል ከመፈረሙ በፊት ረቂቅ የዉል ሰነዱ ከመንግስት መስሪያ ቤቱ ጋር ትይዩ ለሆነዉ በየደረጃዉ ለሚገኝ የፍትህ ቢሮ መስሪያ ቤት ቀርቦ ሕጋዊነቱ መመርመርና መመዝገብ አለበት፤ ዝርዝሩ በመመሪያ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

5/ Except for those specified in the directives issued by the Bureau as not requiring review, before signing any procurement contract, the draft contract document must be submitted to the Bureau of Justice at each level, which is located parallel to the public body, for review and registration of its legality; the details will be determined in accordance with the directives.

፶፭. ውልን ይፋ ስለማድረግ

ከሚስጥራዊ ግዥዎች በስተቀር ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የግዥው ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ውሉ ከተፈረመ በኋላ በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት ወይም በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች መሠረት ዋና ዋና መረጃዎችን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

55. Disclosure of Contracts

Except for confidential procurements, any public body shall disclose key information to the public through electronic systems or other means of communication after the contract for the purchase or sale of property to be disposed of is signed.

፶፮. የውል ማስከበሪያ

፩/ አቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥው ለውሉ ማስከበሪያ የሚሆን የዉል ማስከበሪያ ዋስትና ለግዥ ፈፃሚው ወይም የሚወገድ ንብረት ሻጭ ለሆነው መሥሪያ ቤት ማስያዝ አለበት፡፡

56. Contract security

1/ The supplier or the purchaser of the asset to be disposed of shall provide a contract security to the procurement entity or the seller of the property to be disposed of.

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የቀረበላቸዉን ዋስትና ትክክለኛ መሆኑን ዋስትና ሰጪዉን አካል አስቀድመው በጽሁፍ በመጠየቅ ማረጋገጥ አለባቸው።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የውል የማስከበሪያ የሚጠየቅባቸው የግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ዓይነቶች፣ የውል ማስከበሪያው ዓይነትና መጠን በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፶፯. የውል አስተዳደር

ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚከተሉትን ዋና ዋና የውል አስተዳደር ተግባራት ማከናወን አለባቸው፡-

፩/ የቅድመ ክፍያ፡-

ሀ) በመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ለአቅራቢው የሚሰጠው የቅድመ ክፍያ መጠን እና ዝርዝር አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ የቅድመ ክፍያ ሊፈፀም የሚችለው አቅራቢው በቅድመ ክፍያ መልክ ከሚወስደው ገንዘብ መጠን ጋር እኩል የሆነ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሲያቀርብ ይሆናል።

ሐ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) መሰረት የቀረበላቸዉን ዋስትና ትክክለኛ መሆኑን ዋስትና ሰጪዉን አካል አስቀድመው በጽሁፍ በመጠየቅ ማረጋገጥ አለባቸው።

2/ Public body shall verify the validity of the security provided to them in accordance with Sub-Article (1) of this Article by requesting in advance in writing from the party that provided the security.

3/ The types of purchases and sales of property subject to the requirement of a contract enforcement pursuant to sub-article (1) of this article, the type and amount of the contract security shall be determined by the directives issued pursuant to this Proclamation.

57. Contract Administration

The details of which shall be determined by a directive issued pursuant to this Proclamation, public bodies shall perform the following main contract administration duities:

1/ Advance Payment:

A) The amount of advance payment to be given to the supplier in the execution of public procurement and its details shall be determined by the directives issued pursuant to this Proclamation;

B) Unless otherwise provided in the directives to be issued pursuant to this Proclamation, prepayment may be made upon the supplier providing an advance payment guarantee equal to the amount of money to be received as prepayment.

C) Public bodies shall verify the validity of the guarantee provided to them pursuant to letter (B) of this sub-article by requesting in writing in advance the guaranteeing body.

፪/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፡-

ሀ) የውልን አፈፃፀም የሚከለክል ወይም የሚያስተጓጉል የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመው በስተቀር ከአቅራቢዎች ወይም ከሚወገድ ንብረት ገዢዎች ጋር የተደረጉ ውሎች በፍጥነት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

ለ) በአቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዢው ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመለየት አቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዢው በውሉ መሠረት ተግባራቱን በወቅቱ መፈፀሙን ተከታትሎ ማረጋገጥ፣

ሐ) የውሉ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ውሉ ተፈፃሚ መሆን የጀመረበትን ቀን መዝግቦ መያዝ እና እንደአስፈላጊነቱ አቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዢው እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፡፡

፫/ የውል አፈፃፀምን መከታተል፡-

ሀ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የውል አፈጻጸምን የሚከታተል የሥራ ክፍል መለየት ወይም የውል ክትትል በተለያዩ የሥራ ክፍሎች በቅንጅት የሚፈፀም በሚሆንበት ወቅት የሥራ ክፍሎቹ ተግባራቸውን በግልጽ እንዲያውቁት ማድረግ ይኖርባቸዋል፣

ለ) የውል አፈፃፀምን የሚከታተለው የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍል አቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዢው በውሉ መሠረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል እና የውል አስተዳደር መረጃውን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት መዝግቦ መያዝ ይኖርበታል

2/ Any public bodies shall:

A) Expedite the implementation of any contract concluded with suppliers or buyers of disposable property unless circumstances preventing or disrupting the performance of the contract arise,

B) Identify the activities to be performed by the supplier or the purchaser of the property to be disposed of and monitor the timely performance of the activities by the supplier or the purchaser of the asset to be disposed of in accordance with the contract;

C) Record the date on which the conditions of the contract are met and the contract becomes effective and notify the supplier or the purchaser of the property to be disposed of as necessary.

3/ Monitoring of contract performance:

A) Public bodies should identify a department responsible for monitoring contract performance or, where contract monitoring is carried out in coordination with different departments; ensure that the departments are clearly aware of their responsibilities.

B) The department of Public body that monitors contract performance must monitor whether the main activities to be performed by the supplier or the purchaser of the asset to be disposed of under the contract are being carried out according to the schedule specified in the contract and record the contract management information in an electronic system;

ሐ) አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በውል አፈፃፀም ወቅት የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ እና በጨረታው ከተወዳደሩ ሌሎች ተወዳዳሪዎች አንፃር ለአቅራቢው የተለየ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም፣

መ) የመንግሥት መሥሪያ ቤት በውል አፈፃፀም ወቅት ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን መለየት እና አገልግሎቶቹ፤ የውል አፈፃፀሙን በሚያግዝ መልኩ መሰጠታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

C) If necessary, the contract may be modified during the execution of the contract, provided that the modification to the contract does not harm the interests of the government office and does not give the supplier a special advantage over other candidators in the bid;

D) The Public body must identify services available from third parties during the execution of the contract and ensure that the services are provided in a manner that facilitates the execution of the contract.

፬/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ሁኔታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ቢሮዉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

4/ The conditions under which price adjustments are made shall be determined by the directives issued by the Bureau pursuant to this Proclamation.

፭/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፡-

ሀ) ከአቅራቢዎች ወይም ከሚወገድ ንብረት ገዥዎች ጋር የተፈረሙ ውሎችና ተያያዥ ጉዳዮች በውሎቹ፤ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት መጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ አለበት፣

ለ) ከአቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዢው እና ከሦስተኛ ወገን ጋር ያሉ ተግባራትን በማጠናቀቅ የውል አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

5/ Any Public body shall:

A) Ensure that contracts and related matters signed with suppliers or purchasers of property to be disposed of are completed in accordance with the conditions set forth in the contracts;

B) The contract performance review should be conducted by completing the activities with the supplier or buyer of the property to be disposed of and the third party.

፮/ ውል በግዥ ፈፃሚው አካልና በአቅራቢው መካከል በተገባው የውል ቃላትና ሁኔታዎች መሠረት ሊቋረጥ ይችላል፡፡

6/ A contract may be terminated in accordance with the terms and conditions of the contract between the procuring entity and the supplier.

፯/ በዚህ አንቀጽ ስር ባልተሸፈኑ ጉዳዮች የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

7/ In matters not covered by this Article, the provisions of the Civil Code may apply as appropriate.

፶፰. የውል አለመግባባቶችን ስለመፍታት

፩/ ከግዥ ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥው መካከል የሚፈጠር ማንኛውም አለመግባባት አግባብነት ባላቸው ሕጎች፣ በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ በሚወጣው መመሪያ እና በውሉ መሠረት መፈታት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚፈፀሙ የግዥና ንብረት ማስወገድ ተግባራት የመንግሥት ተቋማት በሚገቧቸው ውሎች የሚፈጠርን አለመግባባት ለመፍታት አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

58. Settling Contractual Disputes

1/ Any dispute arising between the Public body and the supplier or purchaser of the property to be disposed of in connection with the execution of a contract for the sale or purchase of property shall be resolved in accordance with the relevant laws, this Proclamation, the directive issued pursuant to this Proclamation, and the contract.

2/ Government institutions may use alternative dispute resolution mechanisms to resolve disputes arising from contracts entered into for procurement and disposal activities carried out pursuant to this Proclamation. The details shall be determined in a directive issued to implement this Proclamation.

ክፍል አሥር

ስለ አቤቱታ፤ይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ አካል

፶፱. አቤቱታ ወይም ይግባኝ ስለማቅረብ

፩/ ከመንግሥት ግዥ ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ ግዥውን በሚፈፅመው ወይም ንብረቱን በሽያጭ በሚያስወግደው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተከናወነው ወይም ሳይከናወን የቀረው ተግባር ይህንን አዋጅ፣ የመንግሥትና የግል አጋርነት አዋጅና ተያያዥ ድንጋጌዎች፣ የአፈፃፀም መመሪያዎቹንና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ይጥሳል ብሎ የሚያምን እና በመሥሪያ ቤቱ አሠራር ምክንያት የደረሰበትን ወይም ሊደርስበት የሚችልን ጉዳት ማሳየት የሚችል ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች በሕጉ በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በኃላፊው ውሳኔ ካልረካ ይህንን አዋጅ መሰረት በማድረግ በሚወጣው ደንብ መሰረት ለሚቋቋመው ይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ አካል ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ ለመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ስለሚቀርብ አቤቱታ እና ለይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ አካል ይግባኝ ስለሚቀርብበት ሥነ-ሥርዓት፤ በቀረበለት ይግባኝ ላይ ስለሚወስዳቸው እርምጃዎች፤ ስለሚሰጣቸው ውሳኔዎች፤ ውሳኔውን ለሕዝብ ተደራሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ፤ውሳኔን በድጋሚ ስለሚታይበትና ስለሚታረምበት፤ ይግባኝ ማቅረብ የማይቻልባቸው ጉዳዮች እንዲሁም ለፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብትን በተመለከተ ይህንን አዋጅ መሰረት በማድረግ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

PART TEN

Complaint, Appeal and Decision-Making Body

59. Submitting a complain or appeal

1/ Any candidates or bidders who believes that the action taken or omitted to be taken by the public body carrying out the procurement or the sale of property to be disposed of violates this Proclamation, the Public-Private Partnership Proclamation and its related provisions, the implementation directives and the conditions specified in the bidding document, and who can demonstrate the damage suffered or likely to be suffered as a result of the office's actions, may, within the time limit permitted by law, file a complain to the head of the office or if he is not satisfied with the decision of the head of the public body may appeal to the appeal and decision-making body established in accordance with the regulations issued pursuant to this Proclamation.

2/ The procedure for filing a complaint with the head of Public body and for filing an appeal with the appeals and decision-making body; the steps to be taken on the appeal; the decisions to be given; the conditions for making the decision accessible to the public; the review and correction of the decision; the cases where an appeal cannot be filed, and the right to file an appeal with the court shall be determined by a regulation issued by the Regional Administrative Council based on this Proclamation.

፷. ይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ አካል ስለማቋቋም

፩/ በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አወጋገድ ላይ የሚቀርብ ይግባኝን አጣርቶ ውሳኔ የሚሰጥ ከፊል የዳኝነት ሥልጣን ያለውና ገለልተኛ የሆነ የይግባኝ አጣሪ እና ውሳኔ ሰጪ አካል፤ ይህንን አዋጅ ተከትሎ በመስተዳደር ምክር ቤቱ በሚወጣ በደንብ ይቋቋማል፡

፪/ ስለ ይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ አካል ተጠሪነት፤ ሰያሜው፤ ስልጣንና ተግባር፤የአባላት ስብጥርና ብዛት፤ አባላት ሰለሚመረጡበት መሰፈርት፤የሚኖራቸው የሙያ ሰነ- ምግባር ደንብ ፤የሚመረጡበት የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ፤የሚኖራቸው ጥቅማ ጥቅም፤ የሚመሩበት የሰብሰባና የአሰራር ሰነ- ስርዓት፤ በመንግስት መስሪያ ቤቶች በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ለይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ አካል ወይም በዚህ አካል ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ስርዓትና ከአባልነት ሰለሚሰናበቱበት ሁኔታ በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ በደንብ ይወሰናል።

ክፍል አሥራ አንድ

የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚቀርብበት እና የሚጣራበት ሥርዓት

፷፩. ለቢሮው ስለሚቀርብ የጥፋተኝነት ሪፖርት

በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገድ ሂደት የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተጫራቾች፣ በአቅራቢዎች ወይም በሚወገድ ንብረት ገዥዎች ሕገ ወጥ የሆነ ወይም ሕጋዊ ጥቅሜን የሚጎዳ ድርጊት ተፈፅሞብኛል ብሎ ሲያምን በጨረታ ሰነዱ ወይም በውል ስምምነቱ መሠረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጥፋተኝነት ሪፖርት ለገንዘብ ቢሮ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ማቅረብ አለበት።

60. Establishment of an Appeals and Decision Making Board

1/ An independent, quasi-judicial, appellate and decision-making body to hear and decide appeals against the implementation of public procurement and the disposal of property; shall be established by a regulation issued by the Administrative Council pursuant to this Proclamation.

2/ The responsibilities of the Appeals and Decision-Making Body; its name; its powers and duties; its composition and number of members; the criteria for the selection of members; the professional code of conduct they must have; the educational background and work experience they must have; their benefits; the procedure for their meetings and procedures; the procedure for appealing decisions made by public body to the Appeals and Decision-Making Body or to a regular court against this body, and the conditions for their dismissal from membership shall be determined by a regulation issued by the Administrative Council.

PART ELEVEN

Procedure For Submission and Disposing of Report of Default

61. Report of Default to be Submitted to the Bureau

When public body believes that an illegal act or act that harms its legal interests has been committed by bidders, suppliers or buyers of disposed property duringthe implementation of public procurement and property disposal processes, it must submit a report of the offense to the Finance Bureau electronically, while maintaining the measures to be taken in accordance with the bidding document or the contract agreement.

፷፪. ቢሮዉ በቀረበለት የጥፋተኝነት ሪፖርት ላይ ስለሚወስዳቸው እርምጃዎች

፩/ ቢሮዉ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የጥፋተኝነት ሪፖርት ሲቀርብለት የጥፋተኝነት ሪፖርት የቀረበ መሆኑን እና የጥፋተኝነት ሪፖርቱን ፍሬ ሀሳብ የሚገልፅ የጽሑፍ ማስታወቂያ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቀረበበት ተጫራች፣ አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ ይልካል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከቢሮዉ የጥፋተኝነት ሪፖርት እንደቀረበበት የሚገልጽ ማስታወቂያ የደረሰው ተጫራች፣ አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ የጥፋተኝነት ሪፖርት ማስታወቂያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፯ (ሰባት) የሥራ ቀናት ውስጥ መልሱን ከደጋፊ የሰነድ ማስረጃ ጋር በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ለቢሮው ማቅረብ አለበት።

፫/ ቢሮዉ የጥፋተኝነት ሪፖርቱን ለመመርመር እና ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የሰውና የሰነድ መረጃዎችን እንዲሁም ከማናቸውም አካል የሙያ ድጋፍ መጠየቅ እና ማግኘት ይችላል።

፷፫. ቢሮዉ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች

፩/ ቢሮዉ የጥፋተኝነት ሪፖርት የቀረበበት ተጫራች ወይም አቅራቢ ከደረሰው ቀን ቀጥሎ ወይም ምላሽ መስጠት ይገባው ከነበረበት የመጨረሻ ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፲፭ (አሥራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የጥፋተኝነት ሪፖርቱን አጣርቶ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቢሮዉ የሚሰጠው ውሳኔ ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡-

62. Measures to be Taken by the Bureau on Receipt of Report of Default

1/ When the Bureau receives a report of misconduct from a public bodies, it shall send a written notice to the bidder, supplier, or purchaser of the property to be disposed of, stating that the report of misconduct has been filed and the outcome of the report of misconduct.

2/ A bidder, supplier or purchaser of the asset to be disposed of who has received a notice from the Bureau stating that a report of guilt has been filed pursuant to sub-article (1) of this Article shall submit his response to the Bureau, together with supporting documents, electronically within 7 (seven) working days from the date of receipt of the notice of the report of guilt.

3/ Where the bureau finds it appropriate to the investigation and resolution of the report of default, it may summon witnesses to appear in person and give oral testimony, order the production of documentary evidence or seek professional assistance from any appropriate body.

63. Decisions to be given by the Bureau

1/ The Bureau shall examine the report of misconduct and issue a decision within 15 (fifteen) working days from the date of receipt of the report of misconduct by the bidder or supplier or from the next day of the last day on which the response was due.

2/ The decision of the Bureau under sub-article (1) of this article may be one of the following:-

ሀ) በሚያደርገው ምርመራ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘውን ተጫራች ወይም አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ በማንኛውም የመንግሥት ግዥ እና የንብረት ሽያጭ ሂደት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ እንዳይሳተፍ የማገድ፣

A) To prohibit a bidder or supplier or a buyer of a asset to be disposed of, who is found default in its investigation, from participating in any public procurement and property sale process for a specific or indefinite period;

ለ) ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘው ተጫራች ወይም አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ ወይም

B) Issue a written warning to the bidder or supplier or purchaser of the property to be disposed of who is found to be at fault, or

ሐ) የቀረበውን የጥፋተኝነት ሪፖርት ውድቅ የማድረግ፣

C) Rejecting the report of default submitted,

፫/ ቢሮዉ ከመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ክስ የቀረበበትና ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም ሌላ ሥልጣን ባለው አካል ታይቶ ጥፋተኛ በመሆኑ የቅጣት ውሳኔ የተሰጠውን ሰው በማንኛውም የመንግሥት ግዥ እና የንብረት ሽያጭ ሂደት እንዳይሳተፍ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ያግዳል፡፡

3/The Bureau shall prohibit, for a specific or indefinite period, any person who has been charged of a crime related to public procurement and property administration by a regular court or other competent body and has been convicted of the crime, from participating in any public procurement and property sale process.

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈፃፀም የክልሉ ፍትህ ቢሮ ጥፋት የፈፀሙ እና ውሳኔ የተሰጠባቸውን ድርጅቶች መረጃ ለቢሮዉ ያቀርባል፡፡

4/ For the implementation of sub-article (3) of this article, the Regional Justice Bureau shall provide information to the Bureau on organizations that have committed violations and for which decisions have been made.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በስምምነት እልባት የሚሰጡበት፣ የጥፋተኝነት ሪፖርት የቀረበበት ድርጅት ጥፋቱን ተቀብሎ ግዴታውን ሲወጣ ወይም ጥፋቱን ሲያርም ቢሮዉ ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ በመመሪያው ይወሰናል፡፡

5/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this article, the procedure for the bureau to make a decision when the disputing parties resolve their issues through amicable settlement, when the organization to which the report of misconduct was submitted admits the misconduct and fulfills its obligations, or when the misconduct is corrected shall be determined by the directive.

፮/ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበለትን የጥፋተኝነት ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ በመስጠት ሂደት በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የተፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ ጉዳዩን ለመመርመር እና እርምጃ ለመውሰድ በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው የሕግ አስፈፃሚ አካል ያሳውቃል፡፡

፯/ ቢሮው ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቀርቡለትን የጥፋተኝነት ሪፖርቶች የሚመረምርበትን እና ውሳኔ የሚሰጥበትን ዝርዝር አሠራር በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፷፬. በቢሮው ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

ቢሮዉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ቀጥሎ ባሉት ፳፩ (ሃያ አንድ) የሥራ ቀናት ውስጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

6/ The Bureau shall, upon examining and deciding on a report of guilt submitted to it pursuant to Sub-Article (1) of this Article, notify the law enforcement body authorized by law to investigate the matter and take action, if it determines that a criminal act has been committed.

7/ The detailed procedures for the Bureau to investigate and make decisions on reports of misconduct submitted to it from public bodies shall be determined by the directive issued pursuant to this Proclamation.

64. Appeal on the decision of the Bureau

A party aggrieved by the decision of the Bureau pursuant to Article 63, Sub-Article (2) of this Proclamation may file an appeal with the Supreme Court of the Region within 21 (twenty-one) working days following the date of the decision.

ክፍል አሥራ ሁለት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፷፭. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

፩/ በማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት በሚወጡት መመሪያዎች መሠረት እንደሁኔታው የግዥ ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸምና ንብረት አስተዳደር ሪፖርት ያላቀረበ ወይም መቅረቡን ያላረጋገጠ፣ ወይም በቢሮዉ የግዥና ንብረት አዲት ግኝት መሠረት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ ወይም እርምጃ መወሰዱን ያላረጋገጠ፣ ወይም የይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ አካል ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ያልፈፀመ፣ ወይም በዚህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ለሕዝብ ይፋ መደረግ ያለባቸውን መረጃዎች ይፋ ያላደረገ ወይም መደረጋቸውን ያላረጋገጠ፣ ወይም የግዥና የንብረት አስተዳደር ሰነዶችን አደራጅቶ ያልያዘ፣ ወይም ንብረት በወቅቱ ያላስወገደ፣ ኃላፊነቱን በአግባቡ ባለመወጣቱ በሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎች ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር ፲፭ ሺህ (አስራ አምስት ሺህ) እስከ ብር ፴ ሺህ (ሰላሳ ሺህ) የሚደርስ አስተዳደራዊ መቀጮ ይቀጣል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚጣል አስተዳደራዊ ቅጣት በእያንዳንዱ ጥፋት ልክ የሚጣል ሲሆን፣ በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣት ከሦስት ጊዜ በላይ አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት የመስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ቢሮዉ ወይም እንደ አግባብነቱ በተዋረድ የሚገኙት የቢሮው መዋቅሮች በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት እንደቅደምተከተላቸዉ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳደር ምክር ቤት ወይም በተዋረድ ለሚገኙ የመስተዳድር አካላት ያቀርባል።

PART TWELVE

Miscellaneous Provisions

65. Administrative penalties

1/ Any person appointed or assigned to any public body who fails to submit or ensure the submission of a procurement plan, procurement performance and property management report, as the case may be, in accordance with this Proclamation and the directives issued pursuant to it, or fails to take appropriate corrective action based on the findings of the bureau's procurement and property audit or fails to ensure that action has been taken, or fails to comply with an order or decision of an appeals and decision-making body, or fails to disclose or ensure that information that should be disclosed to the public is disclosed in accordance with this Proclamation and the directives issued pursuant to it, or fails to organize and maintain procurement and property management documents, or fails to dispose of assets in a timely manner, shall be liable to an administrative fine ranging from Birr 15,000 (fifteen thousand) to Birr 30,000 (thirty thousand) for failure to properly discharge his duties, without prejudice to his liability under other relevant laws.

2/ An administrative penalty imposed pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be imposed for each offense, and the Bureau or the hierarchical structures of the Bureau, as appropriate, shall submit a report to the Amhara National Regional State Administrative Council or to the hierarchical administrative bodies, as appropriate, for appropriate action to be taken against the head of public body who has been imposed an administrative penalty more than three times for failing to fulfill the obligations imposed by law.

፫/ ቢሮዉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ያስፈፅማል፣ ይህንን ለማስፈፀም የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም "የተመደበ ሰው" ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የግዥ እና/ወይም የንብረት አስተዳደር ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ ክፍልን እንዲመራ የተመደበ የሥራ ኃላፊ ነው፡፡

3/ The Bureau shall implement the administrative penalties imposed in accordance with sub-articles (1) and (2) of this Article and shall issue detailed directives for their implementation.

4/ For the purpose of Sub-Article (1) of this Article, person employed by a public body means a person entrusted with the responsibility of directing the procurement and/or property administration units of a public body.

፷፮. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

66. Power to Issue Regulation and Directive

፩/ የክልል መስተዳደር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

1/ The Regional Administrative Council may issue Regulation when deemed necessary to implement this Proclamation.

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ እንደተጠበቀ ሆኖ በመደበኛ የግዥ መመሪያ መፈፀም የማይቻልበት ሁኔታ ሲፈጠር፤ ክልላዊ የደህንነትና የፀጥታ ጉዳዮችን በተመለከተ፤ወረርሽኝ ሲያጋጥም፤ ግዙፍ ፕሮጅክቶችን በልዩ ሁኔታ ለመፈፀም ሲፈለግ፤ ወይም ሌሎች አሰገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥሙ የግዥዎችን ልዩ ባህሪያት ከግምት ውስጥ በማስገባት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ልዩ የግዥ አፈፃፀም ወይም ንብረት አስተዳደር ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ Without prejudice to sub article 1 of this article, in cases where it is impossible to implement the regular procurement directive; in cases of regional security and safety issues; in the event of an epidemic; when it is necessary to implement large projects under special circumstances; or in other compelling circumstances, the Regional Administrative Council may issue special procurement implementation or property management regulations, taking into account the special characteristics of the procurement.

፫/ ቢሮዉ ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጣ ደንብን ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

3/ The Bureau may issue directives to assist in the implementation of this Proclamation or regulation issued under Sub-Article (1) of this Article.

፬/ ቢሮዉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶች፤ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፤ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራትን ወይም የሰራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት በተመለከተ ልዩ ባህሪያቸውን ከግምት በማስገባት ልዩ የግዥ አፈፃፀም ወይም ንብረት አስተዳደር መመሪያ ሊወጣ ይችላል።

4/ The Bureau, in consultation with relevant parties, may issue special procurement implementation or property management directive for water and sewage service organizations; government development organizations; micro and small associations or job creation institutions, taking into account their special characteristics.

፷፯. የተሻሩና ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎች

67. Repealed and Inapplicable laws

፩/ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፱/፪ሺ፫ ዓ.ም እና የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የከተማና የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶችን እንደገና ማደራጃ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፩/፪ሺ፲፮ ዓ.ም መሰረት የግዥና ንብረት አስተዳደርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተሸረው በዚህ አዋጅ ተተክተዋል።

1/ The provisions relating to procurement and property administration pursuant to the Amhara National Regional State Procurement and property administration Proclamation No. 179/2011 and the Amhara National Regional State Urban and Rural Water and Sewerage Services Reorganization Proclamation No. 291/2024 as amended, are hereby repealed and replaced by this Proclamation.

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

2/ Any proclamation, regulation, directive or customary practice that is contrary to this Proclamation shall not apply to matters covered by this Proclamation.

፷፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

68. Transitory Provision

፩/ ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት ተጀምረው አዋጁ በፀደቀበት ዕለት ያልተጠናቀቁ የመንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሥራዎች ወይም ክርክሮች በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፱/፪ሺ፫ ዓ.ም እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ።

1/ Public procurement and property administration activities or disputes that were initiated before the effective date of this Proclamation and were not completed on the date of its approval shall be resolved in accordance with the Public Procurement and property Administration Proclamation No. 179/2011 and the rules and regulations issued pursuant to the Proclamation.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፰ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ደንብ እስከሚያወጣ ድረስ የሚነሱ የግዥና ንብረት ሽያጭ አቤቱታዎች ወይም የሚቀርቡ ይግባኞች በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፱/፪ሺ፫ ዓ.ም እና ይህን ተክትሎ በወጡ መመሪያዎች መሰረት የሚፈጸሙ ይሆናል።

፫/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም በተሻረው አዋጅ መሠረት የወጣው ደንብ እና መመሪያዎች እንደቅደም ተከተላቸው በአዲስ ደንብ ወይም መመሪያዎች እስኪተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

፬/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የወጡ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎች ይህንን አዋጅ ተክትሎ ቢሮው በሚያወጣቸው ልዩ መመሪያዎች እስኪተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት በማናቸው ውም ሁኔታ ይህ አዋጅ ከሚጸናበት ጊዜ ጀምሮ መመሪያዎች ከስድስት ወር በላይ ሊቆዩ አይችሉም።

፷፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ታህሳስ 17/ 2018 ዓ.ም

አረጋ ከበደ ለጋስ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚደንት

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article 1 of this Article, until the Regional Administrative Council issues regulations in accordance with Sub-Article 2 and Sub-Article 8 of Article 59 of this Proclamation, any complaints or appeals regarding the sale of property shall be governed by the Public Procurement and Property Management Proclamation No. 179/2011 and the directives issued thereafter.

3/ Notwithstanding the provisions of Article 67, Sub-Article (2) of this Proclamation, the regulation and directives issued pursuant to the repealed Proclamation shall continue to be in force until they are replaced by new regulation or directives, respectively.

4/ Notwithstanding the provisions of Article 67, Sub-Article (2) of this Proclamation, the procurement and Property management directives issued by development organizations owned by the regional government shall continue to be in effect until they are replaced by special directives issued by the Bureau pursuant to this Proclamation.

5/ The provisions of sub-articles 3 and 4 of this article shall not, under any circumstances, be in force for more than six months from the date of the enactment of this proclamation.

69. Effective Date of the Proclamation

This proclamation shall come into force from the date of its publication in the Official Gazette of the Amhara National Regional State.

Bahir Dar

December 25/ 2025

Arega Kebede Legas

President of the Amhara National Regional State